



ኢየሩሳሌም ከ6-10ኛው፡ ክፍለ ዘመን፡

# ሐመር




አቡነ ተክለ ሃይማኖት መጀሪያ አጽማቸው አርፎበት በነበረው መካነ አሰቦ በተባለው ቦታ እንደ ጸለዩ ።

ቁጥር 44

ግንቦት፡ ፲፱፻፸፫ ዓ.ም.

www.ethiopianorthodox.org

"ይህ መጽሔት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፣ ሥርዓትና ዜና ፣ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ጭምር እንዲተረጐሙ ለሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ "ትንሣኤ" ተብሎ ተሰይሟል ።

አዘጋጅ
ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ
ም/አዘጋጅ ራድ አስረስ ።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
ሐዋርያዊ ድርጅት
የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ
በወር አንድ ጊዜ
እየታተመ የሚወጣ ።

የስልክ ቁጥር 116616
የመልእክት ሣ.ቁ. 3137
አዲስ አበባ

## ማውጫ

| አርእስት | ገጽ |
|---|---|
| ደብዳቤዎች ............ | ፩ |
| ስፍራ አዘጋጅላችሁ ዘንድ እሄዳለሁ............ | ፪ |
| ቅዱስ ሲኖዶስና ርክበ ካህናት ............ | ፫ |
| መምህር ገብረ ጊዮርጊስ............ | ፬ |
| የምእመናን ድምፅ ............ | ፯ |
| የኤርምያስ ጉድጓድ እንደ ገና ተገኘ ............ | ፱ |
| ምን እንርዳዎ? ............ | ፲ |
| ልደታ ለማርያም ............ | ፲፪ |
| ምሥጢረ ክህነት ............ | ፲፬ |
| ፍልስተ አጽሙ ለተክለ ሃይማኖት............ | ፲፭ |
| የመቃብር ሐውልት ጥቅሙ ምንድን ነው ? ............ | ፲፯ |
| ክርስቲያኖች ለአዲሱ ኅብረተ ሰብእ ............ | ፲፰ |
| የቤተ ሰብእ ዓምድ ............ | ፳ |
| ይህን ያውቁ ኖረዋል?............ | ፳፩ |
| ልማት በቤተ ክርስቲያን ............ | ፳፫ |

# ደብዳቤዎች

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

ከግእዝ ነጠላ ቃላት ላይ ተመሥርተው ወደ አማርኛና ግእዝ ብዙ ቃላት ሲለወጡ ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚያስፈልጋቸው ቃላት እንዳሉ በትንሣኤ መጽሔት የተለየ ዓምድ የተዘጋጀላቸው ሊቃውንት "ሊቅ" የሚለው ቃል በግእዝ "ሊቃውንት" በአማርኛ "ሊቆች" ተብሎ እንደሚበዛ ጠንቅቀው አስተምረዋል ።

የትንሣኤን መጽሔት አዘውትሬ ስከታተል "ሊቃውንቶቻችን" የሚል ርእስ ተደጋግሞ ሲጻፍ በማየቴ ምን አልባት ውሎ አድሮ ይስተካከል ይሆናል የሚል ግምት ነበረኝ ፤ ግን እስከ አሁን አልተስተካከለም ። እንደ ሊቃውንቱ የግሥና የነባር ርባታ ከሆነ መባል የሚገባው በግእዝ "ሊቃውንታችን" በአማርኛ "ሊቆቻችን" እንጂ ሊቃውንቱ ያላስተማሩት በሊቃውንቱ ዓምድ ላይ ተደጋግሞ ሲጻፍ በመጽሔቱ ደንበኞችና አንባቢያን ዘንድ ተለምዶ እንዳይቀር በወቅቱ ይስተካከል እላለሁ ።

መርሐ ጽድቅ ገ ማርያም
ከማኅደረ ስብሐት ልደታ
አ.አ.

መርሐ ጽድቅ ገ ማርያም ስለ ጻፉልን አስተያየት እናመሰግናለን ።"ሊቃውንቶቻችን" የሚለው አነጋገር የተለመደ አነስተኛ ጸያፍ ስለሆነ አላተኰርንበትም ነበር እንጂ ልክ አለመሆኑን ሳንገነዘበው አልቀረንም ። እርስዎም እኮ በግእዝ "ሊቃውንታችን" ተብሎ ይበዛል ያሉት ልክ አይደለም ትክክለኛው ግን ከላይ እንደጠቀሱት በግእዝ "ሊቃውንት" በአማርኛ "ሊቆች" በዝርዝር አመላካች ሲገለጥም ግእዙ "ሊቃውንቲነ" አማርኛው "ሊቆቻችን" ይላል እንጂ በግእዝ "ሊቃውንታችን" የሚል አይኖርም ።

ቢሆንም ይህ አስተያየት የቀረበልን ከእርስዎ ብቻ ሳይሆን ከሌሎችም አንባብያን ስለደረሰን የእርስዎንና የሌሎቹንም አስተያየት በመቀበል "ሊቃውንቶቻችን" በሚል ርእስ ይቀርብ የነበረው ዓምድ "ዜና ሊቃውንት" በሚል ርእስ እንዲቀርብ ተደርጓል ።

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

በመጋቢት ወር በወጣው ቁጥር 42 ትንሣኤ መጽሔት ዲያቆን ጥላሁን ገብሬ "አንድ ሰው ሣሚመተ ዲቁና ከመቀበሉ በፊት ምን ምን ማድረግ አለበት?" ሲል ለጠየቀው ጥያቄ ስትመልስ "ዓይን አይቶ የማያዳላ ፣ ትዕግሥተኛ ...... ብዙ የማይጠጣና የማይሰክር መሆን አለበት ።" ብለህ መልሰሃል ። ነገር ግን ለእኔ እንደሚመስለኝ አንድ ሰው መጠጥን ከቀመሰ በየቀኑ እየቀጠለ ስለሚሄድ እንዴት ከስካር ሊድን ይችላል ?

2ኛ የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር በመጽሐፍ ቅዱስ የሚያምነው እንዴት ነው ? እንደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ነው ? ወይስ እንደሌሎቹ አብያተ ክርስቲያናት ይህን ጥያቄ ለማቅረብ ያሳሰበኝ በትንሣኤ መጽሔት በየወሩ በሚወጣው የመጽሐፍ ቅዱስ ውድድር ሥር ያለው አድራሻ የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ስለ ሚል የኦርቶዶክስ አይደለም ብለው ስለተከራከሩኝ ነው ።

3ኛ/ ቤተ ክርስቲያናችን በየገዳማቱ የምታስተምራቸውን መነኮሳት ትምህርታቸውን ሲጨርሱ ሥራ ታስይዛለች ወይስ ዝም ብላ ትለቃቸዋለች ?

4ኛ/ ቤተ ክርስቲያናችን ሰማንያ አንድ ቅዱሳት መጻሕፍት አሏት ይባላል እኛ አሁን የምንማርባቸውና የምናውቃቸው 66 መጻሕፍት ብቻ ናቸው ። የቀሩትን እንድናውቃቸው ቢደረግ ችግሩ ምንድን ነው? ።

5ኛ/ የቤተ ክርስቲያናችን ታሪክ እየተባዛ ለምን አይሰጠንም ? ይህን ለማድረግ ምን ችግር አለ ?

6ኛ የመጽሔታችሁና የጋዜጣችሁ ተከታታይ ለመሆን እፈልጋለሁ ። ግን መጽሔቱና ጋዜጣው እኔ ወደ ምኖርበት አካባቢ አይደርስም ስለዚህ እንዴት ልከታተል እችላለሁ ?

7ኛ በጠቅላይ ቤተ ክህነት የወጣቶች ጉዳይ መምሪያ ኃላፊ በየመንፈሳውያን ወጣት ማኅበራት እየተዘዋወሩ ለምን ችግሮችን አይመለከቱ ?

8ኛ ቅዳሴ ስንት ዓይነት አለው ?

9ኛ በጾም ወቅት ዓሣ መብላት ይፈቀዳል ወይስ አይፈቀድም ?

10ኛ ሰው ከመነኮሰ በኋላ ምን ማድረግ አለበት ?

ተሾመ ካሣሁን ፦

ተሾመ ካሳሁን ጥያቄዎን ተመልክተነዋል ።

ስለ1ኛው ጥያቄ መጻሕፍት የማይሰክር አብዝቶ የማይጠጣ ይላሉ እንጂ ፈጽሞ የማይጠጣ አይሉም ። ስለዚህም መጠጥ ለቁመተ ሥጋ ያህል ተፈቅዶአል ፤ ግን ራሱን የማይቆጣጠር ከሆነ መስከር ቀርቶ ሌላም ማድረግ ስለሚችል እንዲህ ዓይነቱ ሰው ራሱን አይገዛምና ለዲቁናም አይበቃም ። መዝ. 103 ፥ 15 ምሳ. 23 ፥ 29 - 35 ።

2ኛው ጥያቄ ደግሞ ስለመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር እምነት ጉዳይ ነው ። የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር አብያተ ክርስቲያናትንና ክርስቲያኖችን በአንድነት ለማገልገል በአብያተ ክርስቲያናት ትብብር የተቋቋመ ድርጅት እንጂ ቤተ ክርስቲያን አይደለምና በእምነት የሚለይበት የለውም ፤

በውስጡ የሚሠሩት የጉባዔ አባላትም ሆኑ ቋጥር ሠራተኞች የሚወከሉትና የሚመረጡት ከልዩ ልዩ አብያተ ክርስቲያናት ሲሆን ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንም የሚወከሉና የሚመረጡ አባላት አሉ ። አሁንም የተመረጡ አባላትና የተወከሉ ሰዎች ይሠራሉ ።

4ኛ ስለ 81 መጻሕፍት ወደፊት በአንድነት ታትመው እንዲወጡ ለማድረግ እየታሰበ ስለሆነ በቅርብ ጊዜ ታትመው እንደሚወጡ ተስፋ እናደርጋለን

5ኛ/ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ... ባዛ የሚሰጠው በኮርስ ለሚሰለጥኑ ነው ። ምክንያቱም እዚያ ሲሰበሰቡ

ወደ ገጽ ፲፯ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

## ርእሰ አንቀጽ

# “ስፍራ አዘጋጅላችሁ ዘንድ እሄዳለሁ” (ዮሐ.14 ፥ 3)

የእግዚአብሔር ወልድ ወደ ዓለም መምጣትና ሰው መሆን እንዲሁም ሕማሙ ሞቱና ትንሣኤው ቀደም ሲል በትንቢት እንደተነገረ በምሳሌ እንደተገለጸ ሁሉ ዕርገቱም በትንቢት ተነግሯል ፡፡

ትንቢቱ እንዲህ ነበር “እናንተ መኳንንት በሮችን ክፈቱ የዘለዓለም ደጆችም ይከፈቱ የክብር ባለቤትም ይገባ” መዝ. 23 ፡ 7” አምላክ በዕልልታ ፥ እግዚአብሔርም በመለከት ድምፅ ዓረገ “ መዝ.46 ፥ 5 “ወደላይ ዓረግህ ምርኮን ማረክህ ፥ ስጦታንም ለሰዎች ሰጠህ” መዝ. 67 ፡ 18 የሚል ነው ፡፡

የተናፈቀ ዘመድ ወይም ወዳጅ በመጣ ጊዜ የደስታ አቀባበል ይደረግለታል መስተንግዶ ይዘጋጅለታል ፥ ወደቦታው በሚመለስበት ጊዜ ግን በቅሬታና በኃዘን አንዳንድ ጊዜም በልቅሶ ይሸኙታል ፡፡ ይህ ሁኔታ በክርስቶስና በተከታዮቹ ተፈጽሞአል ፡፡

እግዚአብሔር ወልድ ወደ ዓለም መጥቶ በሰው ባሕርይ የሚገለጥበትን ጊዜ ይናፍቁና ይጠባበቁ የነበሩ ብዙዎች ነበሩ ጊዜው በደረሰና ወደ ዓለም በመጣ ጊዜ አዳኝነቱን ያመኑ ሁሉ በፍጹም እምነት በደስታ ተቀበሉት ትምህርቱን ተአምራቱን ተካፈሉ ፡፡ በተለይም መቶ ሃያው ቤተ ሰብእ (አሥራ ሁለቱ ሐዋርያት፥ ሰባ ሁለቱ አርድእትና ሠላሳ ስድስቱ ቅዱሳት አንስት ) ጌታ ከዋለበት እየዋሉ ከአደረበት እያደሩ ትምህርቱን ተምረዋል ተአምራቱን አይተዋል ፡፡

ታዲያ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሞትን ድል አድርጎ ከተነሣ በኋላ የማዳን ሥራውን ፈጽሞ በሚያርግበት ጊዜ “ወደ ላከኝ እሄዳለሁ ከእናንተም ወዴት ትሄዳለህ ብሎ የሚጠይቀኝ የለም” ዮሐ. 16 ፡ 5 በማለት ሲነግራቸው ቀደመዛሙርቱ አዘኑ ፥ ሲራቡ ኅብስት አበርክቶ የሚመግብ ሲታመሙ የሚፈውስ ትምህርት ተአምራት የሚያደርግ አምላክ ይቅርና ሌላም ተራ ሰው ቢሆን እንኳን አብሮ ሲኖር ከቆየ በኋላ ሲለይ እጅግ ያሳዝናል ፡፡ ሦስት ዓመት ከሦስት ወር እያስተማረና የማዳን ሥራውን እያከናወነ ከኖረ በኋላ በሞት ሲለያቸው እጅግ አዝነው ነበር ግን ሞትን ድል አድርጎ በመነሣቱ ደስታቸው እፁፍ ድርብ ሁኖ ሳለ በዕርገት የሚለያቸው መሆኑን ሲነግራቸው አዘኑ ፡፡ እርሱም “ልባችሁ አይታወክ በእግዚአብሔር እመኑ በእኔም ደግሞ እመኑ በአባቴ ቤት ብዙ መኖሪያ አለ … ስፍራ አዘጋጅላችሁ ዘንድ እሄዳለሁ ፡፡ ሄጄም ስፍራ ባዘጋጅላችሁ እኔ ባለሁበት እናንተ ደግሞ እንድትሆኑ እመጣለሁ ወደ እኔም እወስዳችኋለሁ ፡፡ “ዮሐ. 14 ፡ 1 -4 እያለ ዕውነተኛ ተስፋ በመስጠት ያጽናናቸዋል ፡፡ ከዚህም ሌላ እኔ እንድሄድ ይሻላችኋል እኔ ባልሄድ አጽናኙ ወደ እናንተ አይመጣምና እኔ ብሄድ ግን እርሱን እልክላችኋለሁ” በማለት ከአረገ ከአሥር ቀን በኋላ የሚሆነውን ተስፋ ነግሮአቸው ዓረገ ፡፡

የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን የማዳን ምሥጢር ስንመለከት በልደትና በትንሣኤ የታየው ደስታ በዕርገት ፍጹም እንደሆነ እንረዳለን ፡፡ ስለ እኛ ሰው ሆኖ በሥጋ የተወለደው እግዚአብሔር ወልድ ባይሞት ሞቶም ባይነሣ ፥ ተነሥቶም ባያርግ ኖሮ ደኅንነታችን ባልተረጋገጠም ነበር ፡፡ ብዙ ሰዎች ስለ ሰው ልጅ ሕይወትና መብት ተጋድለዋል ፥ ቢሆንም ሞተውና ተረስተው ቀርተዋል ፡፡ በውነት ስለ ሰው ልጆች ደኅንነት ራሱን መሥዋዕት አድርጎ ያቀረበው ክርስቶስ ግን ሞትን ድል አድርጎ ተነሣ ከተነሣም በኋላ በአርባኛው ቀን ዓረገ ፡፡ ለዘለዓለም በድል አድራጊነት ይኖራል ፡፡

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በየት መቼና እንዴት ዓረገ ? ለሚለው ጥያቄ በሉቃስ ወንጌል 24 ፡ 50 - 5! በሐዋርያት ሥራ 1 ፡ 1 - 11 ባለው ክፍል ተብራርቶ ተጽፎአል ፥ ይኸውም መቼ ዓረገ ለሚለው በተነሣ በአርባኛው ቀን ፥ በየት ለሚለው በቢታንያ እንዴት ለሚለው ደቀ መዛሙርቱ እያዩት እርሱም እየባረካቸው በዝማሬ መላእክት በብሩህ ደመና ዓረገ ፡፡ ብሩህ ደመና የባሕርይ ክብሩ እንደሆነ ሊቃውንት ያስረዳሉ ፡፡

የክርስቶስ ዕርገት ምእመናን ሁሉ በክብር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት የሚያደርጉ መሆናቸውን ያስረዳል “የጻድቃንን ዕርገት ያስረዳ ዘንድ ዓረገ” ተብሎ ተጽፎአልና ፡፡ ዓለምን ለማዳን ሰው የሆነው እግዚአብሔር ወልድ በፈቃዱ ሞተ ሞቶ እንዳልቀረ ለማረጋገጥ ተነሣ ፥ ከተነሣም በኋላ የት እንደሄደ ለማጠየቅ ሰዎችና መላእክት እያዩት በክብር ወደ ሰማይ ዓረገ የተነሣውና ያረገው እርሱ ራሱ እንደሆነ ሲያርግ ያዩት ሁሉ መስክረዋል ፡፡ ሰዎች እያዩት እንደ ዓረገ ዳግመኛ ሰዎች እያዩት እንደሚመጣ እናምናለን ፡፡ “ስፍራ አዘጋጅላችሁ ዘንድ እሄዳለሁ … እኔ ባለሁበት እናንተ ደግሞ ትሆኑ ዘንድ እመጣለሁ ወደ እኔም እወስዳችኋለሁ” በማለት የተናገረ እርሱ እውነተኛ ነውና ፡፡



# ቅዱስ ሲኖዶስና ርክበ ካህናት

ሲኖዶስ ማለት ጉባዔ ማለት ነው ፡ ጉባኤውም በመንፈሳዊ አገልግሎት በኩል ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን የሚተላለፈውን ሕግና ሥርዓት በማውጣት በመወሰን ለቤተ ክርስቲያን አማኞች ሁሉ የሚያሰራጭ ነው ፡፡ እንዲሁም ርክበ ካህናትም ማለት ከቅዱስ ሲኖዶስ የተለየ ዓላማ አይኖረውም ፥ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች የሆኑ ካህናት በአንድ ላይ ተሰብስበው ተመካክረውና ተወያይተው ለችግራቸው መፍትሔ ለመስጠት ሕግ አውጥተው በውሳኔ ካጸደቁ በኋላ ለቅዱስ ሲኖዶስ ለማቅረብ የሚችሉበት ስብሰባ ማለት ነው ፡፡

ካህናቱ የርክበ ካህናት ዕለት የሚነጋገሩትና የሚወያዩት ቤተ ክርስቲያንን ስለሚመለከት መንፈሳዊ ነገር ብቻ በመሆኑ ለሕዝበ ክርስቲያኑም ተስማሚ ይሆናል ይህም ርክበ ካህናት የተባለው ዕለት የሚውለውም ትንሣኤ በዋለ በ 24 ቀን ሲሆን ዕለቱም ከረቡዕ እንዳይወጣ በሊቃውንቱ ተደንግጓል ፡፡

ቀደም ሲል ካህናት በዚህ ዕለት ስብሰባ በማድረግ ስለአጽዋማት ፡ ስለበዓላትና ለመሳሰሉት ቤተ ክርስቲያን ነክ ችግሮች በሰፊው ይወያዩ ነበር ፥ ተወያይተውም ለችግራቸው መፍትሄ ያስገኙ ነበር በአሁኑ ጊዜ ርክበ ካህናት ስሙ እንጂ ሥራው የተዘነጋ ይመስላል ፡፡

ቅዱስ ሲኖዶስም በዓመት ሁለት ጊዜ ከሚያደርጋቸው ዓበይት ስብሰባዎች አንደኛው ስብሰባ በርክበ ካህናት ዕለት እንዲጀመር ራሱ ቅዱስ ሲኖዶስ ወስኗል እስኪ መለስ እንበልና ስለ ቅዱስ ሲኖዶስ አመሠራረትና አመጣጥ ታሪክን እንመልከት ፡፡

የመጀመሪያው ሲኖዶስ የተወጠነው የመጀመሪያው ተመራጮች በሆኑት በሐዋርያት ነው ክርስቶስ ለስብከተ ወንጌል የመረጣቸው ሐዋርያት አሥራ ሁለት ነበሩ የተመረጡትም በክርስቶስ ቃል ብቻ ስለነበር አስፈላጊውን መሪያ ለማግኘት የሚችሉት ከዚያው ከመራሔቻቸውና ከፈጣሪያቸው ከክርስቶስ ብቻ ነበር ሐዋርያት በዚህ ዓለም ላይ ሳሉ ስለሚገጥማቸው ፈተናና ከመካከላቸውም አንዱ እንደሚከዳቸውም ነግሯቸው ነበር ፡፡

በክርስቶስ ቃል መሠረት የአስቆሮቱ ሰው ይሁዳ ለስብከተ ወንጌል ተመርጦ ሳለ ለዓላማውና ለተግባሩ ብቁ ሆኖ ባለመገኘቱ አዳኙንና ፈጣሪውን ለሰለሳ ብር ሲል አሳልፎ ለአይሁድ ከሰጠው በኋላ የሺያዉን ዋጋ 30 ብር ተቀብሎ አልተጠቀመበትም ኢየሱስ በአይሁድ እጅ ተይዞ ሲሠቃይ ባየው ጊዜ አዝኖና እርሱን ተውልኝ የሰጣችሁኝ ገንዘብ እንኩ ተቀበሉኝ ሲል አይሁድን ጠየቃቸው እነርሱም እኛ ለአንተ የምትፈልገውን ገንዘብ ስጥተንሃል አንተም ለእኛ የምንሻውን ኢየሱስን አስይዘኸናል እንግዲህ ወዲህ አንተ ከእኛ እኛ ከአንተ ምን ጉዳይ አለን?የተቀበልከውን ገንዘብ ከፈለግኸው አድርሰው እንጂ አንቀበልህም ስላሉት ሰላሳውን ብር ከእቴናው ላይ በትና ሕይወተ ሥጋውን አሳልፏል ፡፡

ወዲያው አሥራ አንዱ ሐዋርያት ጉባኤ አደረጉና ሁለት ሰዎችን መርጠው ከጸለዩ በኋላ ዕጣቢጥሉ ዕጣው ለማትያስ ወጣና በይሁዳ እግር ተተክቶ ከአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት እንደ አንዱ ተቆጠረ ይህም የመጀመሪያው የሐዋርያት ሲኖዶስ ነበር የሐ. ሥራ 1-26 ፡፡

ከዚያ በኋላ ሐዋርያት ይህንን ዓለም በዕጣ ተካፍለው በንቃትም በትጋት ወንጌልን ሲያስተምሩ አማንያን እጅግ በጣም እየበረከቱ ይሄዱ ጀመር ነገር ግን ከስብከተ ወንጌሉ ጋር የአስተዳደሩ ሥራ ስላስቸገራቸው በሥራ የሚረዷቸውን ሰዎች ለመምረጥ ሲኖዶስ አደረጉና በመጸለይ ሰባት ሰዎችን መርጠው ዲቁና ሾመው እንዲያገለግሉ አድርገዋቸዋል ይህም ሁለተኛው የሐዋርያት ሲኖዶስ መሆኑ ነው የሐ.ሥራ 6.2-6 ፡፡

ሐዋርያት በእነዚህ በተጠቀሱት ጉባዔያት ብቻ ሳይወሰኑ ሌሎችንም ጉባዔያት በማድረግ በርካት ያሉ ውሳኔዎችን አስተላልፈዋል ከሁሉም ጉባዔያቸው ከፍተኛ ደረጃ የሚጠቀሰው እንደ አውሮፓ ዘመን አቆጣጠር በ49 ዓ.ም. የተደረገው ጉባኤ ነው ፡፡

ይህ ሲኖዶስ የተደረገው በተገዘሩትና ባልተገዘሩት ሰዎች መካከል ተነሥቶ በነበረው አለመግባባት ምክንያት ነበር ሐዋርያት በኢየሩሳሌም ተሰብስበው ከተወያዩ በኋላ አስፈላጊው ተግባር በክርስቶስ ስም አምኖ ከተጠመቁ በኋላ መልካም ሥራ መሥራት እንጂ የሥጋን ሸለፈት መገረዝ(ቆርጦ መጣል)ብቻ እውነተኛ የክርስቶስ ተከታይ ሊያሰኝ አለመቻሉን በውሳኔያቸው አጽድቀው ሁሉም በመካከላቸው ያለውን አለመግባባት አስወግደው በክርስቶስ ያመኑ ሁሉ በስምምነት መኖር እንዳለባቸው በሲኖዶሳቸው ውሳኔውን አስተላልፈዋል ይህም ሲኖዶስ የሐዋርያት ሲኖዶስ በመባል በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ታሪክ ዓምድ ተመዝግቦ ይገኛል ፡፡

ከልደተ ክርስቶስ ጀምሮ እስከ አለንበት ክፍለ ዘመን ድረስ ያሉት ዓመታት 1973 እ.ኢ.አ. ሲሆን በሦስት ዓበይት ክፍሎች ተከፍለው ይነገራሉ እነርሱም ከአንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን እስከ አራተኛ መቶ ክፍለ ዘመን ሁለተኛው ከአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን እስከ አንድ ሺህ አራት መቶ አምሳ አንድ ዘመን ያለው ሲሆን ሦስተኛው ደግሞ ከአንድ ሺህ አራት መቶ አምሳ አንድ ዘመን ጀምሮ እስከ አለንበት ክፍለ ዘመን ያለው ዘመን ነው ፡፡

በእነዚህ በተጠቀሱት ዘመናት ሰባት ዓለም አቀፍ የአብያተ ክርስቲያናት ጉባዔያት ተደርገዋል ጉባዔያትም የተደረጉባቸው ዓመታትና ቦታዎች የሚከተሉት ናቸው ፡፡

እንደ አውሮፓ ዘመን አቆጣጠር

ወደ ፰ኛ ገጽ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

# መምህር ገብረ ጊዮርጊስ ገብረ እግዚእ

መምህር ገብረ ጊዮርጊስ ገብረ እግዚእ በትግራይ ክፍለ ሀገር በተንቤን አውራጃ ደብረ ኢየሱስ በተባለው ቀበሌ በ1888 ዓ.ም. ተወለዱ ፡ 12 ዓመት ሲሆናቸው ልዩ ስሙ "እንዳጨጌ" በተባለው ገዳም መንፈሳዊ ትምህርት መማር ጀመሩ 18 ዓመት ሲሆናቸው ለመዓርገ ቅድስናየሚያበቃውን ትምህርት ስለአጠናቀቁ በእንዳጨጌ ገዳም ሥርዓተ ምንኩስና ተቀበሉ ። ቀጥለውም መዓርገ ቅስና ተቀብለዋል ።



ታላቁ ሊቅ መምህር ገብረ ጊዮርጊስ እኒህ ነበሩ ።

ከፍተኛ የትምህርት ፍላጐት ስለነበራቸውየትውልድሀገራቸውን ትተው ከአደጉበት ገዳም ወጥተው ወደ ደብረ ዓባይ በመሄድ መዝገብ ቅዳሴ ተምረው በመምህርነት ተመርቀዋል ፤ ቀጥለውም ወደ ወሎ ክፍለ ሀገር ሄደው በዋግ አውራጃ ዓምደ ወርቅ በተባለው ደብር አለቃ መንበሩ ከተባሉት የቅኔ መምህር በቅኔ መምህርነት ተመረቁ ።

የቅኔ መምህር ከሆኑ በኋላ በጐንደር ክፍለ ሀገር ደብረ ታቦር መድኀኔ ዓለም ከሐዲስ ተክሌ (በኋላ አቡነ ዮሐንስ) የወንጌልና የፍትሐ ነገሥት ትርጓሜ ተማሩ ። ሐዲስ ተክሌ ወደ አዲስ አበባ ሲሄዱ መምህር ገብረ ጊዮርጊስ በዚያው አውራጃ በእስቴ ወረዳ መካነ ኢየሱስ ወደ ተባለው ታላቅ የጉባኤ ቦታ ሄደው ከመምህር ወልደ ሚካኤል ትርጓሜ ሐዲሳትና ዳዊት ተማሩ ቀጥለውም የሐዲስ ተክሌ መምህር ከነበሩትና በዚያው በመካነ ኢየሱስ ነዋሪ ከሆኑ ከመምህር እንግዳየሁ የሃያ ሰባቱን መጻሕፍተ ሐዲሳት ትርጓሜ ከልሰዋል ።

ከዚህ በኋላ ትርጓሜ ሐዲሳትን ፤ ፍትሐ ነገሥትን መላልሰው በተማሩበትና በተመራመሩበት በመካነ ኢየሱስ ወንበር ተክለው ጉባኤ አስፋፍተው ቅኔና ትርጓሜ መጻሕፍት የማስተማር ሥራቸውን ጀመሩ ። በዚህ ሁኔታ በማስተማር ላይ እንዳሉ በ1928 ዓ.ም.ጠላት ኢትዮጵያን በወረረ ጊዜ መምህር ገብረ ጊዮርጊስ በርከት ያሉ ቀደመዛሙርትን አስከትለው ወደ በለሳ ሄደው በዚያ ከነበሩት ኢትዮጵያውያን አርበኞች መካከል ከደጃዝማች ዳኘው ተሰማና ከደጃዝማች አስፋው ተሰማ ጋር በመሆን አርበኞችን እያጽናኑ ወንጌልን በማስተማር ሕዝቡን ለጠላት እንዳይገዛ ለነፃነቱን እንዲጋደል በማስተማር ሀገራቸውን አገላግለዋል ።

ከአምስት ዓመት የአርበኝነት ዘመን በኋላ ኢትዮጵያ በጀግኖችዋ መሥዋዕትነት በእግዚአብሔር አጋዥነት ነፃነትዋን ስትጐናጸፍ በወሎ ክፍለ ሀገር በላስታ አውራጃ ማይ ማርያም በተባለችው ደብ ር ለሁለት ዓመት ከአስተማሩ በኋላ በዚያው ሀገር በወረኢሉ አውራጃ ደብረ ንግሥት በምትባል ደብር ሁለት ዓመት አስተምረዋል ።

በ1940 ዓ ም ቀደም ሲል ያስተምሩበት ወደነበረውና ለጉባኤ አመች ወደሆነው ወደ መካነ ኢየሱስ ተመልሰው ጉባኤያቸውን አስፋፍተው ማስተማራቸውን ቀጠሉ። መምህር ገብረ ጊዮርጊስ ከጠላት በፊትም ሆነ ከጠላት በኋላ በመካነ ኢየሱስ ያስተምሩ በነበሩበት ወቅት በደቀመዛሙርት ብዛት በጉባኤው ስፋት ተወዳዳሪ አልነበራቸውም ።


መምህር ገብረ ጊዮርጊስ በመካነ ኢየሱስ በማስተማር ላይ በነበሩበት ዘመን "ሲያስተምር ለዋለ መምህር ጽዋ ውሃ አንድ እንጀራ ይገባዋል" በተባለው መሠረት ከደብሩ ይከፈላቸው የነበረው ደመወዝ በጣም አነስተኛ ስለነበረ በትምህርት ቤቱ ለመማር የሚመጡትን ዓይነሥራውንና አካለ ስንኩላን ተማሪዎች ለመርዳት የማያስችላቸው መሆኑን ተረድተውና ተማሪዎቹንም ራሳቸውእየረዱ ለማስተማር ስለፈለጉ ተክል እየተከሉ ጐመን እየዘሩ በሚያገኙት ምርት በርከት ያሉ አካለስንኩላንን እየረዱ ያስተምሩ ነበር ።

መምህር ገብረ ጊዮርጊስ መካነ ኢየሱስ ያስተምሩ በነበሩበት ወቅት በቤተ ክርስቲያኑ አካለቢ የተከሉት በመቶ የሚቆጠር የጌሾ ተክል አሁንም ለቤተክርስቲያኑ መገልገያና በቦታው ለሚኖሩ ደካሞች መርጃ በመሆን ከፍተኛ አገልግሎት እየሰጠ ነው ። መምህር ገብረ ጊዮርጊስ "በእናንተ ዘንድ ያለ ሥርዓት አልሄድንም ከእናንተ ዘንድ በአንዱ ስንኳ እንዳንከብድበት ሌሊትና ቀን በድካምና በጥረት እየሠራን እንኖር ነበር እንጂ ከማንም እንጀራን እንዲሁ በከንቱ አልበላንም ። ይህም እኛን እንድትመለሱ ራሳችንን እንደ ምሳሌ እንሰጣችሁ ዘንድ ነበር እንጂ ያለ ሥልጣን ስለሆን አይደለም ። ." 2ኛ ተሰ. 3፥ 8 የሚለውን ሐዋርያዊ ቃል በሥራ የተረጐሙ ዕውነተኛ ሐዋርያና የቤተ ክርስቲያን አባት ነበሩ ።

መምህር በመንፈሳዊና በቀለም ትምህርት ብቻ ሳይሆን በልማት ሥራም ድርሻቸውን ፈጽመዋል ስለፈጸሙትም መልካም አገልግሎት ለሊቃውንት የሚገባውን ሽልማት በጊዜው ከነበሩት ባለሥልጣናች ሁለት ጊዜ ተሸልመዋል ።

መምህር ገብረ ጊዮርጊስ በመካነ ኢየሱስ እጅግ በጣም ሰፊ የሆነ ጉባኤ ዘርግተው ቅኔና ትርጓሜ መጽሐፍ በማስተማር በርከት ያሉ የቅኔና የመጽሐፍ መምህራንን ለቤተ ክርስቲያን አበርክተዋል በዚያው የጉባኤ ቦታ በትምህርት ከወለዷአቸው መምህራን መካከል አንደኛው መምህር ፍሥሐ ጽዮን አሁን ብፁዕ አቡነ በርተሎሜዎስ የሲዳሞ ሀገረ ስብከት ጳጳስ ናቸው ።

መምህር በ1954 ዓ.ም በብፁዕ አቡነ ዮሐንስ የትግራይ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ አነሳሽነት ወደ አክሱም ጽዮን ተዛውረው በአክሱም ቅዱስ ያሬድ መንፈሳዊ ት/ቤት የአክሱም ጽዮን የቅኔና የመጽሐፍ መምህር ሆነው ለሃያ ዓመታት ያህል በማስተማር እያሌ ሊቃውንትን አፍርተዋል ። በቅኔና በመጽሐፍ መምህርነት ከመምህር ገብረ ጊዮርጊስ ተመርቀው የወጡትን መምህራን ቁጥር ዘርዝረን ለማቅረብ ስለማይቻል ቤተ ክርስቲያን ትቁጠራቸው በማለት እናልፈዋለን ።



መምህር ገብረ ጊዮርጊስ ከደቀ መዛሙርት ጋር

መምህር ገብረ ጊዮርጊስ በ1961 ዓ.ም ወደ ኢየሩሳሌም ሄደው ቅዱሳት መካናትን ተሳልመው ከአበው ጋር ተነጋግረውና በዚያ የሚገኙትን ምእመናን አጽናንተው ተመልሰዋል ።

መምህር ወደ አክሱም ከመሄዳቸው በፊት በመካነ ኢየሱስና በሌሎች አድባራት ለአርባ ዓመታት በአክሱም ለሃያ ዓመታት ያህል በጠቅላላ ለስድሳ ዓመታት አስተምረዋል ። መምህር ገብረ ጊዮርጊስ በቃል የሚያስተምሩትን በተግባር እየገለጡ በማስተማር መልካሙን ሩጫቸውን ከፈጸሙ በኋላ በ85 ዓመት ዕድሜያቸው ጥር 1 ቀን 1973 ዓ.ም ዓርብ ከቀኑ በ11 ሰዓት ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል ።

የሊቁ ዕረፍት እንደ ተሰማ ሊቃውንት አክሱም ተሰብስበው ከምሽቱ 3 ሰዓት ሲሆን አስከሬናቸው ከጉባኤ ቤታቸው ወጥቶ ወደ አክሱም ጽዮን ቤተ ክርስቲያን ተወሰደ ። በ5 ሰዓት የቤተ ክርስቲያኑ ቀኝና ግራ ደወል ተደውሎ ቀሳውስቱ ሰዓታት መዘምራኑ ማኅሌት ቆሙ ሊቃውንቱ በሙሉ በተገኙበት ሙሉ የአደራረስ ሥርዓተ ፍትሐት ሲደርስላቸው አደረ ። በአደራረሱ ከተለያዩ ሊቃውንት በረከት ያሉ የተለያዩ ቅኔያት ተደርሰዋል ። ሥርዓተ ፍትሐቱ ከዚህ በላይ በተገለጸው ሁኔታ ከተፈጸመ በኋላ ቅዳሜ ጥዋት በ3 ሰዓት ጥር 2 ቀን 1973 ዓ.ም. ማለት ነው ቅዳሴ ተቀድሶ ድርገት ሲወርዱ ነጋሪት እየተጐሰመ መጥቅዕ እየተመታ ሊቃውንቱም "ወተቀበልዎ መላእክት በስብሐት........ ወአብዕዎ ኢየሩሳሌም ሰማያዊት" የሚለውን ያሬዳዊ መዝሙር እየዘመሩ አስከሬናቸው ልብሰ ተክኅኖ በለበሱ ካህናትና መዘምራን እየታጀበ ወደ ተዘጋጀለት መካነ መቃብር ተጉዞ በአክሱም ጽዮን ቤተ ክርስቲያን የቀብራቸው ሥነ ሥርዓት ተፈጽሞአል ።

መምህር ገብረ ጊዮርጊስ መካነ ኢየሱስ ያስተምሩ በነበሩበት ጊዜ በጉባኤ ከዘረፉአቸው ቅኔዎች ሁለት መወድሶችን እናቀርባለን ቅኔዎቹ አንዱ በዓቢይ ጾም በደብረ ዘይት ሳምንት ነገረ ምጽአትን አስመልክተው የዘረፉት ሲሆን 2ኛው ግን የተማሩበትና የሚያስተምሩበት መካነ ኢየሱስ በተዋህዶ ሃይማኖት የተመሠረተ አራቱ ጉባኤያት የሚነገሩበት ታላቅ ድብር መሆኑን ለማስረዳት በማኅሌት የተቀኙት ነበር ።

ቅኔዎቹ 1ኛ

ኩሉ በዓለ አመ ይገብር
ይጼውዕ ሰብአ ዐቢየ ወርኡሰ ።
እንዘ እግአዜ ያከብር ወያስተዋርድ
ጽኑሰ ።
ዜና ኢዮስያስ ቀዳማዊ
ከመ ይሑር ሎቱ አኮኑ ;ኃሠሠ ።
ወበጽርሐ በዓል ኢሐወሰ
ዘይፈድይዎ ክብረ ዕውረ ወሐንካሰ ።

ለዓለም

ደብረ ዘይትስ ሶበ ገብረ በዓለ ምሳሌ
መቅደሰ ።





www.ethiopianorthodox.org

ኢሉለየ በጸውያ ዐቢየ ወንኡስ ፡፡
ለእመ ነዳየ ኮነ ወእመ ኮነ ንጉሠ ፡፡
እስመ ስምዓ በጉባኤ ብሉየ ወሐዲስ ፡፡

ትርጓሜው (ፍችው)

ሰው ሁሉ በዓል (ጉብኘ) በአደረገ ጊዜ ችግረኛውን እያኖረደ ባለጸጋውን እያከበረ አለቃውንና ታላቁን ይጠራል የቀደመው የኢዮስያስ ዜና ይሰራጭለት ዘንድ ፈልጎአልና፡፡በበዓሉ (በግብዣው) አዳራሽም ክብር የሚያሰጡትን ዕውርንና አንካሳን (ደካሞችን- አላስታወሰም ፡፡

ደብረ ዘይት ግን የምሳሌ በዓልን በመቅደስ ባደረገ ጊዜ በጥሪው ታላቅና ታናሹን አልለየም ችግረኛ ወይም ንጉሥ ቢሆን በጉባኤ ብሉይንና ሐዲስን ሰምቶአልና ፡፡
2ኛ መካነ ኢየሱስ ታቦር ልዑል አድባር እስመ በውስቴቱ ከሠተ ምሥጢረ ዓቢይ መለኮቱ
እግዚእ ምናሴ ወኤፍሬም ድልወ ኒቅያ ሥርዓቱ ፡፡
ዕበየ ኒቅያስ ይትናገሩ ፣
ኤልያስ ወሙሴ ጽውዓን ውስቴቱ ፡፡
ሙሴ ወኤልያስ
እስመ ሰማዕተ ደብር ኮኑ ምስለ ሐዋርያት ሠለስቱ ፡፡

ለዓለም

ቤተ ጽድቅሂ ቤተ ሥላሴ መካነ ኢየሱስ ውእቱ ፡፡
እስመ ኢያንቀለቅል ለዓለም ሃይማኖት መሠረቱ ፡፡
ባሕቱ ድልው መልዕልተ ሰማያት ስብዓቱ ፡፡
መካነ ኢየሱስ መንበረ አብ ዘይጸውርዎ አርባዕቱ ፡፡ ፍችው (ትርጓሜው)

መካነ ኢየሱስ ፣ የአድባራት ከፍተኛ ታቦር ነው ፣ ሥርዓቱ የተዘጋጀ የምናሴና የኤፍሬም ጌታ ከፍተኛ የሆነ የመለኮቱን ምሥጢር (ሃይማኖትን) በውስጡ ገልጦአልና፡፡ ተጠሩ ኤልያስና ሙሴም የኒቂያን ክብር ይናገራሉ ፡፡ ሙሴና ኤልያስ ከሦስቱ ሐዋርያት ጋር የደብር (የተራራ) ምስክሮች ሆነዋልና ፡፡

መካነ ኢየሱስ የጽድቅና የሥላሴ ቤት ነው ፡፡

ሃይማኖት መሠረቱ ለሁልጊዜ አይናወጥምና ፡፡ ነገር ግን አራቱ ጉባኤያት የሚሸከሙት የአብ ዙፋን መካነ ኢየሱስ በሰባቱ ሰማያት (ሰባቱ ምሥጢራት) ላይ የተዘጋጀ ነው ፡፡

ይህ ቅኔ የሚገልጠው መካነ ኢየሱስ በተዋህዶ ሃይማኖት የተመሠረተ ፣ በተዋህዶ ሃይማኖት የጸና ፣ አራቱ ጉባኤያት የሚነገሩበት መሆኑን ነው ፡፡

3ኛ/ በአንድ ታላቅ ዓመት በዓል በተቀኙት ዕጣነ ሞገር ቤተ ክርስቲያንንና ተዋህዶ ሃይማኖትን አስመልክተው የተቀኙትን ቅኔ ከዚህ በታች እንመለከታለን ፡፡

በእደ ኬንያ ማርቆስ አመ ተሐንጸ ሃይማኖተ ወንጌል ማኅፈድ ፡፡
እንዘ ደብረ ድማኅ ጠፈር መካነ ኢየሱስ ዓምድ ፡፡
እስመ በውስቴቱ ኢይወርድ ፡፡
ውኂዘ ማኒ ዕልው ወንስጥሮስ ካህድ ፡፡
ኅበ ጸንዓ መሠረት ወልድ ፡፡
ትርጓሜው (ፍችው)

የወንጌል ሃይማኖት አዳራሽ በመሐንዲሱ በማርቆስ እጅ በታነጸ ጊዜ ደብረ ድማኅ ጠፈር (ጣራ) ሲሆን መካነ ኢየሱስ ዓምድ (ምሰሶ) ነው ፡፡ ወልድ መሠረት ከጸና ዘንድ የንስጥሮስና የማኒ ፍሳሽ ጥርጥር በውስጡ አይወርድም ፡፡

የቅኔ ሙያ ኃዘንን እንደ ኃዘንነቱ ፡ ደስታንም እንደ ደስታነቱ ፣ ሁሉንም እንደሁኔታው ለመግለጽ ፣ ለማመስገንም ሆነ ሂስ ለማቅረብ የሚያስችል ልዩ ጥበብ ነው ስለሆነም ባለሙያዎቹ ደስታቸውንም ሆነ ኃዘናቸውን ፣ ቅሬታቸውንም ሆነ ሂሳቸውንና ችግራቸውን ሲገልጹበት ኖረዋል አሁንም ይገልጹበታል ፡፡ መምህር ገብረ ጊዮርጊስም መጽሐፍትን አዘውትረው ከመመልከታቸው የተነሣ ዓይናቸውን ይታመሙ ነበር በአንድ ዘመን በተከታታይ ሦስት ጊዜ እጅግ በጠና ስለታመሙና ዓይናቸውም ሆነ መላ ሕይወታቸው በጣም ስለተዳከመ የሚከተለውን መወድስ ዘረፉ ፡፡

በሙኑ አተልል ከበደ ተግናየ
ጽኖን ሕማም ወሞት ትኅልፍ እምኔየ፡፡
እምጣነ ከህደኒ ሥልስ ሐዋርያ ብርሃን ዓይንየ ፡፡
ወኅፀተ ባሶር ሠረገላ
መጽአ ከመ ይስቅለኒ ሰናክሬም ደዌየ፡፡
ሠራዊተ ባቢሎን አመ ርእየ ፣
እስመ ጸበበቶ ምድር ሏሕዝቅያስ ሕሊናየ ፡፡

ለዓለም

ኃይልየሂ ወልደ ዕሴይ ለእመ ረሥዓ ወበልየ ፡፡
ነግሠ በፈቃዱ አዶንያስ ሕማምየ ፡፡
ወእመ ትትገፈታዕ ሥልስ ኢየሩሳሌም ሥጋየ ፡፡
ተንሥእ ለተሰዶ ዕንባቆም ልቡናየ ፡፡

ፍችው (ትርጓሜው) የሕማምና የሞት ጽኖ ከእኔ ትወገድ ዘንድ የመገፋትን ክብደት በማን አቀላለሁ የብርሃን ሐዋርያ ዓይኔ ሦስት ጊዜ ከዶኛልና ፡፡በሽታዬ ሰናክሬምም በሥጋ ጉድለት ሠረገላ ይሰቅለኝ ዘንድ መጣ ፡፡ የባቢሎንን ሠራዊት ባየ ጊዜ ለሕዝቅያስ ሕሊናዬ ምድር ጠብባዋለችና ፡፡

የዕሤይ ልጅ ኃይሌም ፈጽሞ ባረጀ ጊዜ ሕማሜ አዶንያስ በፈቃዱ ነገሠ ፡፡ ኢየሩሳሌም ሥጋዬም ሦስት ጊዜ በሕማም በተገለባበጠች ጊዜ ዕንባቆም ልቡናዬ ለመሰደድ ተነሣ ፡፡ በማለት ኃዘናቸውን ገልጠው ነበር ፡፡

---



# የምእመናን ድምፅ

ይህ አምድ የኢትዮጵያ ኦ.ተ.ቤተ ክርስቲያን በአስተዳደር ተሐድሶ የምትራመድበትና የምትኘኝበት ክርስቲያኖች ስለ ቤተ ክርስቲያናቸው በቀና መንፈስ አስተያየት የሚያቀርቡበት ነው ፡፡ በዚህ ዓምድ ሲቀርቡ የሚገባቸው ጽሑፎች የቤተ ክርስቲያናችን ውሳኔዎች ሳይሆኑ የግለሰቦች አስተያየት መሆናቸውን የዓምዱ ተከታታዮች በቅድሚያ እንዲያውቁልን እንፈልጋለን ፡፡

አዘጋጅ ነቅዓ ጥበብ ወንድም የስልክ ቁጥር 11-66-16 የመልእክት ሣ.ቁ. 3137 አዲስ አበባ

## ክርስቲያኖች ከአሥር አንድ ሊከፍሉ ይገባልን ?

በብሉይና ሐዲስ ኪዳናት ውስጥ ለእግዚአብሔር ስጦታን በማቅረብ ከሚያገኙት ሁሉ ከአሥር አንድ በመስጠት ምሳሌ የሆኑ ግለ ሰቦችና ማኅበሮች ብዙዎች ናቸው ፡፡

ለምሳሌ በቡሉይ ኪዳን ያዕቆብ ወደ አባቱ ቤት እግዚአብሔር ቢመልሰውና ቢጠብቀው የሚበላውንና የሚለብሰውንም ቢሰጠው እግዚአብሔር ከሰጠው ሁሉ አስራት እንደሚሰጥ ተሳለ ፡፡

ይሁን እንጂ የያዕቆብ አሥራት አስተዋጽኦ ስለ ሦስት ዋና ዋና ምክንያቶች ነው ፡፡ ሀ- ስለ ጤና እግዚአብሔር በጤና ቢመልሰኝ ለ/ስለ ጥበቃው ( እግዚአብሔር ቢጠብቀኝ ) ሐ/ ስለ ፍላጐት መሟላት ነበር ታዲያ እግዚአብሔር ለእኛስ እነዚህን ነገሮች አሳጥቶን ያውቃልን?

የያዕቆብን የአሥራት ስጦታ ስንመለከት ከሙሴ ሕግ በፊት በነበሩት አባቶች ዘመን አሥራት መስጠት የተለመደ እንደነበር እናስታውሳለን ዘፍ.28 ቁ22

በሐዲስ ኪዳንም ክርስቲያኖች ስለ ልዩ ልዩ ብዙ ምክንያቶች የአሥራትና የፈቃድ ስጦታ ያደርጋሉ ከብዙዎቹ መካከል ሀ- ለአምልኮተ እግዚአብሔር ለ- አገልጋዮችን ለመንከባከብ ሐ-ለትምህርተ ወንጌል ሙ-ነዳያንን ለመርዳት እንደነበር ግልጽ ነው ፡፡

ዛሬም አንዳንድ ክርስቲያኖች ይህን በተግባር እንደሚተረጉሙት ይታወቃል በአሁኑ ጊዜ በምእመናን ድምፅ አምዳችን እንዲህ ያሉትን በጎ አድራጊዎች ለመግለፅ ስለፈለግን የሚያውቁትን



አቶ ፋንታዬ ይመር

እንዲያብራሩልን አቶ ፋንታዬ ይመርን ጠይቀናል ፡፡

ጥያቄ ፣አንዳንድ ክርስቲያኖች በክርስትና ሕይወት በኩል ያላቸው እንቅስቃሴ በጣም ጉልሕ ሆና ይታያል ፡፡ ይህን ን ሊያደርጉ የቻሉት ከትምህርት በሚያገኙት ጥናት ወይስ ከወላጆቻቸው ባገኙት መልካም አስተዳደግ ይመስልዎታል ?

መልስ ፣ -እንደ ጥያቄው አባባል አንዳንድ ክርስቲያኖች ይህን መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ሲፈጽሙ የሚታዩት በመልካም አስተዳደግ፣ከጥሩ መምህራን በተማሩት ትምህርትና በእግዚአብሔር ፈቃድና ምህረት ጭምር፣ይመስለኛል፡፡ይህንንም የሚያደርጉ ክርስቲያኖች ለዚህ እድል መርጦ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ባርነት ነፃነት ባወጣቸው አምላክ ያመልካሉ 1ኛ/ ቆር.ም. 1ቁ. 29-31 ዮሐንስ ወንጌል ም.6 ቁ44-65፡፡ ጥያቄ ፦ መጽሐፍ ቅዱስ ክርስቲያኖች ከአሥራ አንድ ለእግዚአብሔር አሥራት እንዲከፍሉ ያዝዛል ግን አብዛኛዎቹ ክርስቲያኖች ይህንን ስላለመዱት አስተዋጽኦ ሲያደርጉ አይታዩም አንዳንድ ክርስቲያኖች ግን አሥራት መክፈል ደስ ይላቸዋል ስለዚህ ምን አስተሳሰብ አለዎት?

መልስ፣- እንደተባለውም አንዳንዶቹ ካለመልመድ የተነሣ አስተዋጽኦ ማድረግ ደስ አይላቸውም ይሆናል አንዳንዶቹ ግን በአምላካቸው ትእዛዝ ትንሽ ሲያወጡ ቀሪውን ገንዘብ በቸርነቱ ስለሚባርከው ይበዛል ፣ ይትረፈረፋል ፣ በተጨማሪም በተሰጠው አሥራት ለእግዚአብሔር አገልግሎት የቆሙ ወንጌላውያን ቃሉን ለሕዝብ ለማዳረስ በየሥፍራው ሲዘዋወሩ በማያስፈልጋቸው ጥቃትን ወጪ ከሚያውሉትም በላይ የሕይወት ቃሉን የሰሙ ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ አምነው በተቀደሰ ዓላማ ሲመሩ ብዙ እኅትና ወንድሞችን ለማግኘት ስለሚቻል በደስታ የተባለውን አሥራት በፈቃዳቸው ይከፍላሉ ዘዳግም ም.14፣22-29

ጥያቄ፦ በውጭ ያሉ ክርስቲያኖች ለወንጌል ማስፋፊያ የሚሆን ገንዘብ ከደሞዛቸው ከአሥር አንድ ይረዳሉ በአገራችን ያልተለመደው ለምን ይመስለዎታል?

መልስ፦ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን የዓለም መድኃኒትና ትንግኤ ሙታን የሚያበስረው ወንጌል ለኢትዮጵያ የተሰበከው በሐዋርያው ፊሊጶስ አማካይነት ከብዙ ዓመታት በፊት መሆኑን የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 8 ቁጥር 27-39 ያ




www.ethiopianorthodox.org

ስረዳል ። ከዚህ በኋላ ወንጌል ከደረሳቸው ክፍለ ዓለማት ጋር የእኛ እርምጃ ሲነጣጠር በጣም ወደ ኋላ መቅረቱ የማይታበል ሐቅ ነው፣ይህም ማለት ካህናቱ ለብዙኃኑ ሕዝብ የወንጌል ትምህርት ባለማስተማራቸው ሲሆን የሚያውቁትንም በዚህ በኩል ያለው አመለካከታቸው በሥልጣን ድጋፍና በፍቅረ ንዋይ ስለተሸፈነ ነው ።

ይህ እንዳይሆን ለሕዝበ ክርስቲያን የወንጌል ብርሃን ለማዳረስ የተማረ የሰው ኃይል እንደሚያስፈልግ ጥርጥር የለበትም የአንድ የሃይማኖት ድርጅት ሥራውን ለማስፋፋት ቢሞክርም በገንዘብ በኩል ያለውን ወጭ ለማሟላት ብቻውን ይወጣዋል ማለት የክርስቲያን ተግባር ባለመሆኑ የምዕመናን ድጋፍ የሚያስፈልገው መሆኑን ክርስቲያኖች ተገንዝበው ከሚያገኙት ከወር ገቢ ገንዘባቸው ከረዱ የወንጌል ብርሃን ለእነሱም ሆነ ለሌሎች ሊያበራ ይችላል የወንጌል ሰባኪም እንደልቡ ሊያስተምር ፈቃደኛ ይሆናል ይህ ተግባር በሥራ ላይ ከዋለ ብዙ ሰዎች የደገፉት በመሆናቸው በተግባሩ ተሳታፊ መሆን ጀምረዋልና ለወንጌል ማስተማር ሥራ ይረዳሉ ብዬ አምናለሁ ።

ጥያቄ፡- ክርስቲያኖች ሁሉ ይህንን አርአያ እንዲከተሉ የመጨረሻ አስተያየት ቢሰጡን?

መልስ ፡- ክርስቲያን ማለት ለእግዚአብሔር የተለየ ቅዱስ ሕዝብ ማለት ነው፣ይህንንም ሥራ ለብቻው ሊጠቀምበት እንደማይገባው በእግዚአብሔር ቃል መማር ይቻላል ፣ የተቀደሰ ሕዝብ ፍቅር፣ሰላም የተጐናጸፈ እኩልነትና ትክክለኛ ፍትሕ የሰፈነበት የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ መድኃኒትነትን አምኖ የተቀበለ በቅንነትና በታማኝነት የሚኖር ሰው መሆኑን አውቆ ወንድሙን እንደ ራሱ የሚወድ በደስታ መንገድ የሚጓዝ የራስ መውደድና የስስት በሽታ የማይታይበት ከመልካም ሥራ በስተቀር ክፉ ተግባርን የሚጠላ የአምላኩን ትዕዛዝ የሚያከብር መሆን አለበት ፣ በዚህ ዓላማም የሚመራ ሁሉ እውነተኛ ክርስቲያን ነውና መሰል ወንድሙ የሰው ልጅ ሁሉ የዚህ ተግባር ተካፋይ እንዲሆን ማድረግ ግዴታው ነው ፣ ይህም አፈጻጸም ሊሟላ የሚችለው ሥጋዬን የበላ ደሜን የጠጣ የዘለዓለም ሕይወት አለው የሚለውን ቃል ሁሉም ሲማር ነው ፣ ለመማርም የሚችለው በዚህ እውነተኛ ዓላማ ጸንቶ የሚኖር ክርስቲያን ካለው ንብረት ከአሥር አንድ ከዚህም በላይ ቢሆን በፈቃዱ አውጥቶ የምሥራቹን ቃል ለሚዘሩ መምህራንና ቤተ ክርስቲያን በመስጠት ሥራው እንዲከናወን ፈቃደኛ ሆኖ ሲገኝ ነው እንጂ ቤተ ክርስቲያን ደርሶ መመለስ ብቻ ሀብትን በመውደድ እያካበትን ብናስቀምጠው የልብ ሳይሆን የስም ክርስቲያን በመሆን፣ መክሊቱን ከደበቀውና ለአደራ ከማይበቃው አገልጋይ ጋር ወደ ፍርድ ያገባናል ፣ ስለዚህ ክርስቲያን ነኝ የሚል ሁሉ ካለው ንብረት ከአሥር አንድ ቢሰጥ ሁሉን ማድረግ የሚቻለው አምላክ እጥፍ ድርብ አድርጐ ሀብቱን ቤተሰቡን እንደሚባርክለት የተናገረው ቃል የታመነ መሆኑን አውቀን በአሥራት ማውጣቱ ተግባር እንሰማራ ፣

በአንዳንድ የሃይማኖት ድርጅቶች ብንሔድ ተስፋፍተውና እርምጃቸውን አስቀድመው የሚገኙት በሚያወጡት ከአሥር አንድ መሆኑን መታወቅ አለበት ።

ይህን አስተያየት የሰጡን አቶ ፋንታዬ ይመርን በትንሣኤ መጽሔት ስም እናመሰግናለን ስለዚህ ክርስቲያኖች ሁሉ ይህን አርአያ ቢከተሉ እግዚአብሔርን አክባሪ ትእዛዙን ፈጻሚ መሆናቸውን እንዲያውቁት እናስገነዝባለን ።

## ቅዱስ ሲኖዶስና ......

ከገጽ ፫ የዞረ

በ325 ዓ.ም. በኒቅያ
2 በ381 ዓ.ም. በቁስጥንጥንያ
3 በ431 ዓ.ም. በኤፌሶን
4 በ451 ዓ.ም. በኬልቄዶን
5 በ553 ዓ.ም. በቁስጥንጥንያ
6 በ681 ዓ.ም.”
7 በ787 ዓ.ም. በኒቅያ ተደርገዋል ።

ከተጠቀሱት ሰባት ጉባኤዎች የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ርክስቲያን የምትቀበላቸው ሦስቱን ብቻ ነው እነርሱም የኒቅያ የኤፌሶን የቁስጥንጥያ ናቸው በእነዚህ በሦስቱ ጉባኤዎች የተወሰኑትን ውሳኔዎች ሁሉ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ያለ ጥርጥር የምትቀበል ስትሆን የቀሩትን ማለት በሌሉች ሲኖዶሶች የተወሰኑትን አትቀበልም ማንኛይቱም ቤተ ርክስቲያን ከተመሠረተች ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ በብቸኝነት አትሠራም የምትሠራው በቅዱስ ሲኖዶስ እያጠናች ነው ከዚህም የተነሣ የቤተ ክርስቲያን ዕድገት የሚወሰነው በቅዱስ ሲኖዶስ አቅም ነው ቅዱስ ሲኖዶስ በሚያደርገው እንቅስቃሴ ቤተ ክርስቲያን ልታድግም ልታንስም ትችላለችና ፣ ቅዱስ ሲኖዶስ በትምህርትም በልማትም በአስተዳደርም ከውጭ ሀገር አብያተክርስቲያናት ባለውም ግንኙነትና በመሳሰሉትም ተግባሮች ጠንክሮ የመሥራት ግዴታ አለበት ። ቅዱስ ሲኖዶስ በርትቶ ከሠራ ቤተ ክርስቲያናችን በዕውቀት ትበለጽጋለች በውስጧም ፍቅርና ሰላም ይጸናሉ እምነቷም የጠነከረ ሀብቷም የተትረፈረፈ ይሆናል ።

ቅዱስ ሲኖዶስ የቤተ ክርስቲያን ዓይን ነው “ዓይንህ ታማሚ ከሆነ መላው ሕዋሳትህ ጨለማ ይሆናል ዓይንህ ብሩህ ከሆነ መላው ሰውነትህ ብሩህ ይሆናል” ብሎ ክርስቶስ እንዳስተማረው ቅዱስ ሲኖዶስ የቤተ ክርስቲያናችን ዓይን ስለሆነ ብርሃናውያን የሆኑ መመሪያዎችን በየጊዜው እያመነጨ ለአብያተ ክርስቲያናት የማሰራጨት ኃላፊነት አለበት የሚያሠራጫቸውም ሕጐች በሚገባ

ተከታዩ ወደ ገጽ ፳፮ ዞርአል



# የኤርምያስ ጉድጓድ እንደገና ተገኘ!

በባርጅል ፒክሰነር አስብ

በ587 ከክር.ልደት በፊት ኢየሩሳሌም በባቢሎናውያን የምትቃትትበት ጊዜ ነበር ይህ ዘመን በነቢዩ ኤርምያስ ላይ አሳዛኙ ታሪክ የተፈጸመበት ጊዜ ነው ። ጠላቶቹ ጉድጓድ ውስጥ በገመድ አሥረው ጣሉት ። በጉድጓድ ውስጥም ውኃ አልነበረም ። ነገር ግን ጭቃ ወይም ፍግ ብቻ ነበር ። ኤርምያስም በጭቃው ተዋጠ ። (ኤር.38፥6) አቤሜሌክ የተባለ ኢትዮጵያዊ የንጉሥ ሴዴቅያስ የጦር መኰንን በሰላሳ (30) ሰዎች እየተረዳ ነቢዩን ከጉድጓድ ጐትቶ አወጣው በረሃብ ከመሞትም አዳነው ።

ከቢዛንታይን እስከ መስቀል ጦርነት ዘመን ተሳላሚዎች አዛውትረው ይጐበኟቸው ከነበሩትና በጣም ከታወቁት የመጽሐፍ ቅዱስ የታሪክ ቦታዎች አንዱ የኤርምያስ ጉድጓድ ነው ። ይህንንም በዘመኑ ወደ ኢየሩሳሌም የተጓዙ ተሳላሚዎች ከተውልን መረጃዎች መጥቀስ ይቻላል ። ከዚያ በኋላ ግን ፈጽሞ የተረሳ ይመስላል ።

አሁን ያለበት ፡- በኢየሩሳሌም የኤርምያስ ጉድጓድ በመባል የታወቀው ስፍራ ዛሬ ፈጽሞ ተረስቷል ። ወደ ምሥራቅ ኢየሩሳሌም የአውቶቡስ ማዞሪያ በሚወስደው ቀጭን መንገድ መጨረሻ የደማስቆ በር በተባለው ያሮጌው ከተማ ሰሜን ምሥራቅ ሊገኝ ይችላል ። የቀሻው ቅርጽ ጥልቀት ያለው የጥንትድንጋይ ሲሆን የጐርደን ቀሻ በመባል የታወቀው ነው ። ያሁኑ ስም መቼ ወይም እንዴት እንደ ተሰጠ የሚያውቅ ሰው ያለ አይመስልም ። በኤርምያስ ዘመን ይህ አካባቢ ከከተማው ግድግዳ ውጭ ሲሆን በቀላሉ የወታደር ቤትና ነቢዩ የተጣለበት ጉድጓድ አልነበረም ።

የቢዛንታይን ጥንታውያን ምንጮች የኤርምያስን ጉድጓድ ወደ ጲላጦስ ወታደሮች መኖሪያ ያስጠጉት ሲሆን፣አንድ አንድ ሊቃውንት ብርከተ እሥራኤል ተብሎ ከሚጠራው ውሃ ጋር አዛምደው ያስቡታል ። የቤተ መቅደሱ የሰሜን ተራራ ወይም በትልቁ ውሃ መያዣ ኤቼ ሖሞ ይህም እንደ ቢዶዛንታይን አቀራረብ ባገኙአቸው የተለያዩ ነቢባት (ቴሪዎች) ላይ የተመሠረተ ነው ።

ጀ ውልክስን ወደ ውነት የተቃረቡ ይመስላሉ ፣ እንደ እርሳቸው አስተሳሰብ በደቡባዊው የከተማ ክፍል መፈለግ አለበት ፣ ምናልባት ከታላላቅ የውኃ ማከማቻዎች አንዱ በደቡብ ምዕራብ ጫፍ አጠገብ በሚገኘው ቤተ መቅደስ አካባቢ ነው ይላሉ ። እርሱም ለጥበብ ቤተ ክርስቲያን ቅርብ ሲሆን በበጐች መዋኛና በሲሎን መካከል ነው ። እርሱም ለአሁኑ ዶንጌት ቅርብ ነው ።

የኤርምያስ ጉድጓድ በፕሪቶሪየም አካባቢ የወታደሮችን ሠፈር አስመልክቶ ከቀረቡት ነቢባት (ቴዎሪዎች) አንዱም እንኳን አያረካም ። ለምሳሌ የኤቼ ሖም ነቢብ ፕሪቶሪየምን በአንቶኒያ የሚያመለክት ወይም በሄሮድስ ቤተ መንግሥት ላይ ያለው የሲድል ነቢብ (ቲዎሪ) ነው ። በ1975 በዚህ ነገር የራሴን ጥናት ጀመርኩ ።

የእኔ ጥናት የሻገታ ማርያ ነያን ቤተ ክርስቲያን በማግኘት አዲስ አቅጣጫ ሰጠ ። የጥናቱ ውጤቶችም በብዙ አገሮች ታትመዋል ባጭሩ ፍሬ ሀሳቦችን አቀርባለሁ ።

ሀ- የእሥራኤል አርኬዎሎጅስቶች የቢዛንታይን ቤተ ክርስቲያን አስጠግተው አቅርበውታል ።

ለ- ከአንዳንድ የጽሑፍ ምንጮች እንደ ተገኘው ሁኔታው ከፕሪቶሪየም ቤተክርስቲያን ወይም ቅድስት ሶፍያ የተጠጋ እንደ ነበረ ግልጽ ነው ይህም በዘመኑ ከተገኙትና ወደ ቅድስት ሀገር ከተጓዙ ምዕመናን ዘገባና ሥርዓተ ቅዳሴው መረዳት ይቻላል።እንዲሁም ከስድስተኛው ክፍለ ዘመን የማዳብ ሞዛይክ ካርታ (ሥዕል) የቢዶዛንታይን ፕሪቶሪ ዛሬ በምዕራብ ግድግዳ ፐላዛ በተባለው አልፎ ወደ አይሁድ ሸንጐ በሚሄደው መስመር መፈለግ አለበት ። እርግጠኛው ቦታ የፓራት ዮሴፍ የሸባ ነው ከነያ ሰሜን-ምሥራቅ ማዕዘን አይርቅም ።

ሐ- በእኔ አስተያየት ባይዛንታውያን ውነተኛ የጥንት ባሕል ይከተላሉ ፣ በሄሮድስ ባድማ የፕሪቶሪየም ቤተ ክርስቲያን ተሠርቷል ፣ እንዲሁም የሕግ አስተዳደር ሸንጐ ወይም የቀድሞውን ሐስምንያን ቤተ መንግሥት ጭምር በ339 ዓ.ም. ቦርዴክስ በጐበኘበት ወቅት የቤተ መንግሥቱ ግድግዳዎች ላዕላይ መዋቅር ታች ወደ ቻይሮፔዎንደርስው ታይተው ነበር ። በእኔ የምርምር ሂደት በፕሪቶሪየም አንድ ካህን ጓደኛዬ የሆኑትን እሥራኤላዊ ተመራማሪ ሜር-ቤን-ደብን አነጋገርኳቸው ። እርሳቸውም የደቡብ ቤተ መቅደስ ግድግዳና የከተማው ምርምር ሃላፊ ናቸው የሶፍያን ቤተ ክርስቲያን በትክክለኛው መስመር ከሆነ “የቢዛንታይን የኤርምያስ ጉድጓድ በዶንጌት አጠገብ መሆን አለበት እርግጠኛውን ቦታ ተረድተዋልን ? አልኳቸው ለትንሽ ጊዜ አሰላሰሉና” አንድ የሚቻልበት መንገድ አለ ። ምን እንደ ምታስብ ናና እይ” አሉኝ ። የዶንጌት ደቡባዊ ምሥራቅ ወደ ሆነው የድንጋይ በር ሃምሳ ሜትር ያህል ተከተልኳቸው በኃይል ከገፋነው በኋላ ደጃፉ ወደ ውስጥ ተከፈተና በውስጡም የዕቃ ክፍል የዛጉ ያልጋ ብረቶች ማቀዝቀዣዎች ማሰሮዎችና ድስቶች አሉበት ። በሻማ ብርሃን እየተረዳን አሥር ሜትር የሚያህል ቁልቁለት ወረድንና ሰፊ ከሆነ ዋሻ ደረስን ዋሻውም በታላላቅ ወጋግራዎች የተደገፈ ነው ። የወለሉ ዝቅተኛው ክፍል ከደረቁ የጭቃ ንብርብሮች (ከጡብ) የተሠራ ነው ። ከዚህ ጉብኝት በኋላ ወደ ጉድጓድ እያሌ ጊዜ በመመላለስ አንድ ጊዜ ባይዛንታውያን አምልኮት ያሳዩበትን ቦታ ልዩ ምልክቶችን አገኘሁ ። በመግቢያው በር ላይ የሚገኘው ልዩ ድንጋይ ለምሳሌ የመስቀል ቅርጽ ነበረው አሁን በከፊል ምልክቱ

ወደ ገጽ ፲፱ ዞርአል



www.ethiopianorthodox.org

# ምን እንርዳዎ ?

ይህ ዓምድ አንባቢዎች ችግራቸውን የሚገልጹበት ፡ ለችግራቸው መፍትሔ የሚሰጡበት ፡ ጥያቄና መልስ የሚያቀርቡበት ስለሆነ ምን እንርዳዎ ተብሎ ተሰይሟል ።




አዘጋጅ ተስፋ ጥሩነህ
ስልክ ቍጥር 11-66-16
የፖ.ሣ.ቁ. 31-37
አዲስ አበባ


ለትንሣኤ መጽሔት ምን እንርዳዎ ዓምድ አዘጋጅ
አዲስ አበባ

ከዚህ የሚከተሉትን ሦስት ጥያቄዎች ታብራሩልኝ ዘንድ እጠይቃለሁ ፡

1ኛ/ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መዝሙር በአማርኛና በግዕዝ እንደሚዘመር የታወቀ ነው ። በመሣሪያውም ፥ በከበሮ በጸናጽል ፥ በመቋሚያ በመጠቀም ነው ፥ ግን በዘመናዊ መሣሪያዎች ማለት በፒያኖና በመሳሰሉት መዘመር ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ውጭ ነውን ?

2ኛ የትንሣኤ መጽሔት ለወጣት ክርስቲያኖች ለምን የተለየ ዓሞድ የለውም? ለምንስ አይከፈትም ?

3ኛ ብዙ ወጣት ክርስቲያኖችን የሚያጨቃጭቅ ነገር አለ ፥ ይኸውም እግዚአብሔር የወደፊቱንና የሚመጣውን እያወቀ አዳምም ዕፀ በለስን እንደሚበላ እየተረዳ ለምን ዕፀ በለስን ተከላት ?

ከዚህ በላይ ያለው ጥያቄ የእኔ የግሌ ሳይሆን በማኅደረ ስብሐት ቅድስት ልደታ የሚገኙት ክርስቲያኖች ጥያቄ ስለሆነ መልሱን በናፍቆት እንጠባበቃለን ።

ደረጀ ቀኖ
ከማኅደረ ስብሐት ቅድስት ልደታ
ወጣቶች መንፈሳዊ ማኅበር
አዲስ አበባ

ደረጀ ቀኖ! ጥያቄውን ተመልክተነዋል ። በ1ኛው ተራ ቁጥር ስለተጠየቀው ፥ በቤተ ክርስቲያናችን በፒያኖና በኦረጋን በመሳሰሉት መሣሪያዎች ቢዘመር የቤተ ክርስቲያንዋን ሥርዓት አያፋልስም ፥ በቤተ ክርስቲያናችንም በነዚሁ መሣሪያዎች መዘመር በተለይ በአዲስ አበባ እየተለመደነው ።

ከበሮና ጸናጽልም እኮ የተገኘው ከመ/ ቅዱስ ውጭ አይደለም ለምሳሌ ሙሴ እስራኤልን እየመራ ከምድረ ግብፅ ባሕረ ኤርትራን ባሻገረ ጊዜ እህቱ ማርያምና ሌሎቹም እየዘመሩ ለእግዚአብሔር ምስጋና ያቀረቡት በከበሮ ነበር ዘፀ.15 ፥ 20

በከበሮና በጸናጽል ብቻ ሳይሆን በመለከት ድምፅ በበገናና በመሰንቆ ፥ በአውታርና በእምቢልታ እግዚአብሔርን ዲመሰገን ታዞአል መዝ.150፥2-5 ፥

ዛሬም ቢሆን የተሻሻለ ድምፅ ባለው መሣሪያ እግዚአብሔር ቢመሰገን የቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓት ስለማይከለክል ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ግዕዙም ሆነ አማርኛው በኖታ ፥ በኦርጋንና በፒያኖ እንዲዘመር እያደረገች ነው ፥ የግዕዙንም ሆነ የአማርኛውን አዘማመር ለማወቅ ቢሹ ለምሳሌ ያህል የሚከተሉትን መዝሙራት ይመልከቱ ።







አዝማች ፤

ፀሀይ ዓመት ለኛ ተንገላታ
ተሰቃይቶ ሞተ ቸሩ የዓለም ጌታ ።
ቸሩ መድኃኔ ዓለም የዓለም ሲሣይ
በመስቀል ላይ ሆነህ አይተሃል ሲቃይ ።

አዝማች ፤

እባክህ ጌታዬ ጨሽቴን ስማኝ
ነፍሴ ተጨነቀች ዕረፍትን ስጠኝ ።
አማኑኤል ቸሩ መዓትህ የራቀ
ይቅርታ አረክልኝ አዳም በወደቀ ።

የአማርኛ መዝሙር በዘመናዊ ኖታ

ስለዚህ በተሻሻለ መሣሪያ እግዚአብሔርን ማመስገን ተገቢ እንጂ የሚከለከል ነገር ስለሌለ እናንተም በዘመናዊ መሣሪያ እየዘመራችሁ እግዚአብሔርን ብታመሰግኑት የበለጠ ነውና በርቱ ።

ስለሁለተኛው ጥያቄ የትንሣኤ መጽሔት የወጣቶች ዓምድ ከፍቶ ስለ ወጣቶች መጻፍ ከጀመረ ዓመታት አልፈዋል የገረመኝ ግን ጥያቄው የወጣቶቹ በሙሉ ነው ተብሏል ። ታዲያ ይህንን ዓምድ አንድ ወጣት እንኳ ሳያየው መቅረቱ ነው ፥ ብቻ በቁጥር 40 ጥር 1973 ዓ.ም. ላይ በተለየ ምክንያት የወጣቶች ዓምድ ሳይወጣ ስለቀረ ያነበባችሁት መጽሔት እርሱ ብቻ ከሆነ ሌሎቹን መጽሔቶች በመከታተል የወጣቶችን ዓምድ ማግኘት ትችላላችሁ ። ሦስተኛው ጥያቄ ደግሞ ብዙ ወጣቶችን ያጨቃጭቃል የተባለው የዕፀ በለስ አበቃቀል ጉዳይ ነው ።

ምድር ዘርን የሚሰጥ ሳርንና ቡቃያን፥ በምድርም ላይ እንደወገኑ ዘሩም ያለበትን ፍሬን የሚያፈራ ዘፍን (ዘፍ1 ፥ 11 - 12)ታብቅል ብሎ እግዚአብሔር ባዘዘ ጊዜ ሁሉም በቀለ በዚሁ ጊዜ የሚመር የሚጣፍጥ ፥ የሚያድን ፥ የሚገድል በአጠቃላይ ሁሉም በቀለ ፥ የሚገድል መርዝ የሞላበት ዕፅ በአዋቂዎች መድኃኒት ሊሆን ይችላል ። በለስም በዚሁ ጊዜ አብራ የበቀለች ዕፅ ናት ።

ታዲያ አዳም በለስን እንደሚበላ ስለሚያውቅ እግዚአብሔር መጀመሪያ ሥርዓት ሲሠራለት በለስን እንዳይበላ አስጠንቅቆታል ። አዳምንም ሲፈጥረው ጐጂና ጠቃሚውን እንዲያውቅ አድርጎ በመሆኑ ይጐዳሀል እያለ እየነገረው ከበላ ደሚም ሆነ ቅጠሏ መድኃኒት የምትሆነውን በለስ እግዚአብሔር ለምን ፈጠረ ማለት አንችልም ፡ ልንልም አይገባም ።

ሰውም የተፈጠረው በነፃ ፈቃድ በትክክለኛ አእምሮ የፈለገውንና የሚፈልገውን ለማድረግ ስለሆነ አታድርግ የተባለውን መለኮታዊ ትዕዛዝ አፍርሶ በለስን በላ ፥ በእግዚአብሔር ቃል መሠረትም ሞት ተፈረደበት ዛሬም ተው ቢሉት የማይተው በመሆኑ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ በማፍረስ አታድርግ የሚባለውን እያደረገ ስለሆነ የመጀመሪያው ሰው ለምን በለስን በላ ? እግዚአብሔርስ ይህንን እያወቀ በለስን ለምን ተከለ ? ልንል አይገባም ።

ዛሬም እንደ ሐሺሽ የመሳሰሉ ጐጂና በአእምሮ ላይ ቀውስ የሚያስከትሉትን ዕፀዋት አትብሉ ሲባል ትእዛዝ ስለሚጥስ ምንም ማድረል አይቻልም ።

ስለዚህ ሰው በተፈጥሮ በተሰጠው አእምሮ በማመዛዘን ጠቃሚውንና ጐጂውን ለይቶ መሥራት አለበትና ዕፀ በለስን እግዚአብሔር ለምን ፈጠረ? ከማለት ይልቅ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ እንዲጠብቅ የተሰጠውን መመሪያ አዳም ለምን ተላለፈ ? ማለት ይቀላል ።

---




www.ethiopianorthodox.org

# የሴቶች ዓምድ

አዘጋጅ ብርሃን ተድላ

## ልደታ ለማርያም

ቅድስት ድንግል ማርያም ለብዙ ዘመን መክነው ይኖሩ ከነበሩ ከደጋግ ቤተሰቦች ኢያቄምና ሐና ከሚባሉ በብፅአት ተወለደች እነዚህም ቤተሰቦች ምንም እንኳ ብዙ ዘመን መክነው ቆይተው ቢወልዱና የልጅም ፍቅር በጸና ቢኖር ባቸው ፍቅሯን እስኪጠግቡ በቤት ሊያቆይዋት አልፈቀዱም ስለዚህም በተወለደች በ3ኛው ዓመት እንደ ብፅዓታቸው ወደ ቤተ መቅደስ ወስደው ለሊቀ ካህናቱ ሰጧት ።

ይሁን እንጂ የመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ልደት እንዲህ ቢሆንም ከሌላው ሰው ልደት የሚለይበትን መንገድ እንጠቁማለን ።

ልዩ ከሚያደርጉት ምክንያቶች ጥቂቶቹ፡ እመቤታችን ማርያም ከመጸነሷና ከመውለዷ በፊት እርሷ ተወልዳ ጌታን እንደምትወልድ ትንቢት ተነግሮላታል ሱባዔም ተቆጥሮላታል ። ምሳሌም ተመስሎላታል ።

ይህም ስለ ክርስቶስ ሰው መሆን ነቢያት ትንቢት ሲናገሩ ሱባዔም ሲቆጥሩ እንዲሁም ስለመቤታችን በሰፊው ተናግረዋል ። ምሳሌም መስለዋል ምሳሌውም ሆነ ትንቢቱ ግን ለጊዜው ግልጥ ያልሆነ ለማን እንደተነገረ ምን ማለት የሆነ ለህዝብ ስውር ሆኖ ይኖር ነበር ። ስለ እርሷም ከተነገሩት ትንቢቶችና ምሳሌዎች ጥቂቶቹን እነሆ ።

ነቢዩ ኢሳይያስ "ድንግል ትፀንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች ሲል ኢሳ.ም. 7 ቁ.14 ተናግሮ ነበር ። ይህም በጊዜው ለማን እንደተነገረ ግልጽ አልሆነም ነበር በኋላ ግን ቅድስት ድንግል እግዚአብሔር ወልድን 9 ወር ከ5 ቀን በማህፀኗ ተሸክማ ስትወልድ የተነገረው ትንቢትና ምሳሌ በግልጥ ታወቀ ለቅድስት ድንግል እንደተነገረም ተረጋገጠ ።

ቅዱስ ዳዊትም "ልዑል እግዚአብሔር ጽዮንን መርጦአታልና ማደርያውም ትሆነው ዘንድ ወድዶአታልና" መዝ. 132 ቁ. 13 ሲል እግዚአብሔር ወልድ በማህፀኗ እንደሚያድር ተናግሯል እንደ ገና ኢሳይያስ ሕግ ከጽዮን ይወጣል የእግዚአብሔርም ቃል ከኢየሩሳሌም "ኢሳ. ም.2 ቁ 3 ብሎ ትንቢት በተናገረ ጊዜ በጽዮን የመሰላት ቅድስት ድንግል ማርያምን መሆኑ በኋላ ተረጋገጠ እንደዚሁም ኢየሩሳሌም ብሎ የሰየማት ቅድስት ድንግል ማርያምን ነበር ።" ከእሴይ ግንድ በትር ይወጣል ከሥሩም ቁጥቋጦ ያፈራል "ኢሳ. ም. 11 ቁ1 ባለ ጊዜ በበትር የመሰላት ቅድስት ድንግል ማርያምን ነው ።" ይህ ከኢዮምያስ ልብሱም የቀላ ከባሶራ የሚመጣ ኢሳ.ም. 6 ቁ 1 ሲል የክርስቶስን ወደዚህ ዓለም መምጣትና ቅድስት ማርያምን ደግሞ በኢዮምያስ መስሏታል ። ነቢዩ ሕዝቅኤልም በበኩሉ "ይህ በር ተዘግቶ ይኖራል እንጂ አይከፈትም ሰውም አይገባበትም የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ገብቶበታልና ተዘግቶ ይኖራል" ሕዝ. 44ቁ2 ሲል በበር (በአንቀጽ) መስሎ ስለ ቅድስት ማርያም ተናገረ ። እዚህ ላይ አትኩረን የምንመለከተው ዘለዓለ ማዊ ድንግልናዋን ግልጽ መሆኑን ነው ። እንባቆምም ደግሞ በበኩሉ "ቅዱስም ከፋራን ተራራ ይወጣል" እንባ ም. 3 ቁ 3 ብሎ ተናግሯል ። የፋራን ተራራ የተባለች ክርስቶስን የወለደች ቅድስት ማርያም ናት ።

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የሰሎሞን አክሊል የአሮን በትር ፡ የዳዊት መሰንቆ የጌዴዎን ፀምር ተብላ ትመሰላለች ።

ነቢዩ ኢሳይያስም "እነሆ እግዚአብሔር በፈጣን ደመና እየበረረ ወደ ግብፅ ይመጣል ወደ ምሥርም ይገባል ። ኢሳ. ም. 19 ቁ.1 ሲል በደመና መስሏታል ። ምክንያቱም የምሕረት ዝናም ጌታን የጸነሰች ቅድስት ማርያም እንደሆነች ለማረጋገጥ የምህረት ዝናም ውኃን የያዙ እውነተኛ ደመና እርሷ መሆኗን ሲገልጽ ነው ።

ከዚህ በላይ በተዘረዘሩት ሁሉ የተመሰለችና ነቢያት ትንቢት የተናገሩላት ሱባዔ የቆጠሩላት ቅድስት ድንግል ማርያም መሆኗ በሐዲስ ኪዳን ተረጋግጧል ። ይህም በገላትያ ም.4 ቁ 4 በተጻፈው መሠረት ነው ።

እንግዲህ የመቤታችን የቅድስት ማርያም የመውለዷ ደስታ የቤተሰቦችዋ ብቻ ሳይሆን አምላክን ወልዳ እኛን ከሞት ወደ ሕይወት ለመሸጋገራችን ምክንያት ስለሆነች የአዳም ልጆች ሁሉ ደስታ ነው ።

ቅድስት ድንግል ማርያምን እኛ ክርስቲያኖች የምንመካባት ከፍጡራን በላይ ከፈጣሪ በታች ናት ብለን የምናምናት የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ እናቱ በመሆኗ ነው ቅድስት ድንግል ማርያም ለሰው ልጅ ደህንነት አሳቢ የሰው የድካሙና የችግሩ ተካፋይ ናት ።



ቅድስት ድንግል ማርያም በተለይ የሴቶች መመኪያ ናት ። ምክንያቱም በሔዋን ስህተት የተዘጋው ገነት በእርሷ አማካኝነት ተከፍቶልናልና ።

ስለዚህ የቅድስት ድንግል የልደቷን በዓል የምናከብረው በተለይ እኛ ሴቶች በአምልኮ ባዕድ ሳይሆን በአክብሮትና በደስታ ፍጹም በሆነ ሃይማኖታዊ ሥነ ሥርዓት መሆን አለበት ።

## የኤርምያስ ጉድጓድ ....

ከገጽ ፱ የዞረ

ለቋል ፡ በበታቹም አጠር ያለ የግሪክኛ ጸሎት የመጀመሪያው መስመርና ግማሹ ብቻ ይነበባል ። ለምሳሌ ይህም ጌታ ሆይ እነርሱን የሚጸልዩትን እርዳቸው የሚል ነው ።

ይህ የምድር ውስጥ ዋሻ በባይዘንታይን ዘመን ለጐብኞች አንድ የተለየ ትርጉም ነበረው ። በሰሚናዊው ግድግዳ መውረጃ ላይ በታላላቅ የግሪክ ፊደሎች ባሉት የእጅ ጽሑፎችም ተረጋግጧል ። ጽሑፉም ሙንጭርጭር ያለ ማለት የምንጽሑፍን ደንብ ያልተከተለ ነበር።

አንድ አንድ የተለያዩ የግሪክ ፊደሎች እሉ ከእነርሱም መካከል አንድ ላንዶቹ ለክርስቶስ የተለዩ ምልክቶች ነበሩ ለምሳሌ ያህል ክርስቶስን ተከተለው የሚል ቃል አለባቸው ። ወደታችኛ ትንሽ ጉድጓድ ያለ ነበር በመግቢያው ክፍል በጣራው አንድ ሰፊ ቀዳዳ አለ ።በመረጃው መሠረት የውኃው ጋን ጥንታዊ አፍና በምሥራቁ ግድግዳ ትልቅ ቀዳዳ በድንጋይ ውስጥ ተቦርቡሯል ። ይህም አንድ ቀዳዳ ሆኖ ለቅዳሴ አገልግሎት ሊሆን ይችላል ። የመውጫው ደረጃ እንደገና በተቆፈረ ጊዜ ነው የተገኘው በማለት ተስፋ ተደርጓል ። ከላይ የተገለጹት ነገሮች ሁሉ በየጊዜው ከተገኙት የጽሑፍ መረጃዎች ጋር በጥሩ ሁኔታ የተዛመዱ ይመስላል ።

የተሳላሚ ሪፖርቶች ፡- መመሪያቸውን ከሴፕቶአጀንት የወሰዱ ሲሆን በግሪክ የኤርምያስ ጉድጓድ ተብሎ ይጠራል ።

ላቲኑም ይህን የግሪኩን ስም እንደያዘ ነው ። ሆኖም የላቲኑ ትርጉም ሐይቅ ወይም ሰፊ የውኃ (ዳር) ጠርዝ ማለት ነው ምናልባት በሚያስገርም የጉድጓድ ስፋት የተደነቁ ይመስላል ።

የዚህን ቦታ በጥንቱ አገላለጽ የላቲን ቃል እናገኛለን አንድ ቴዎዶስዮስ የተባለ ሰው በ520 ዓመተ ምህረት በእርሱ የቅድስት ሀገር ጠቅላላ አገላለጽ ከአንድ ቅዱስ ቦታ ወደ ሌላው ያሉትን ርቀቶች ዝርዝር ይሰጠናል ። ከፕሪቶሪየም ቤተ ክርስቲያን በመጥቀስ ይጽፋል ፡ ባካባቢው ቅዱስ ኤርምያስ ወደ ጉድጓድ ተጥሎ ነበር ። የዘመዶቹ ዕርቀታቸው (ሲገመገም በመሠረቱ ከሁኔታው ጋር ይነፃፀራል ከቅድስት ጽዮን እስከ ኬፋ ቤት ድረስ አሁን የጴጥሮስ ቤተ ክርስቲያን ተብሎ የሚጠራ ሲሆን ሃምሳ እርምጃዎች ያህል ነው ። ከኬፋ ቤት እስከ ጲላጦስ ወታደሮች ቤት ድረስ አንድ መቶ እርምጃዎች ያህል ነው ። ነቢዩ ኤርምያስን በጣሉበት ጉድጓድ የሴሎም ባሕር አንድ መቶ እርምጃዎች ይርቃል ። እርሱም በግድግዳው ውስጥ ነው የኢየሩሳሌምን ከተማ የሚገልጽ የመመሪያ መጽሐፍ ከ510-540 ዓ.ም ተጽፏል ። ጉድጓዱን ይገልጻል ። በፕሪቶሪየሙ አካባቢ ከከተማው ወደ ሲሎም በሚወስደው መንገድ ነበር ፡ ከሃምሳ ዓመታት በኋላ አንድ ተሳላሚ ከሰሜን ኢጣልያ ከፕየጩንሳ ቅድስት ሀገርን ጉበኝ የጉዞዎቹ ዘገባ በ570 ዓ.ም የተቀረጸው የመዳብ ሥዕላዊ ሪኮርድ በጥሩ ሁኔታ ያብራራል ። የጽዮንን ተራራ ትቶ ወደ ሰንታ ማርያ ኑያ ቤተ ክርስቲያን መጣ በብዙ አልጋዎችና ጠረጴዛዎች የተደራጁ ሆስቴልና ሆስፒታል የተከበበ ነበር ። ከዚያም በፕሪቶሪየም (ሰንታ ሶፍያ) ጸለየ ሪፖርቱ ይቀጥላል ።

ከዚያም ከስፍያ የአሮጌው ከተማ በር ወደ ሆነው የደጃፍ ማዕዘን መጠን በዚህ ኤርምያስን በጣሉበት ቦታ በብዙ ደረጃዎች ወደ ሴሎም ትወርዳላችሁ ይህን የዓይን ምስክር ሪፖርት ከመዳባ ሥዕላዊ መግለጫ ጋር ብናወዳድርና በቅርብ ጊዜ ተቆፍረው የተገኙትን አንዳንድ ፍንጮች ብንከተል ፡ ለፓርሺያውያን ወረራ ቅድሚያ በመስጠት ለዶንጌት አካባቢ ጠቅላላ ሁኔታ አያሌ ማጠቃለያዎችን ማቅረብ እንችላለን ።



በመጀመሪያ እንደ ማዳባ ሥዕላዊ ዘገባና የተሳላሚ አቆጣጠር ፡ የካርድ ቫሌንሲስ መኖር አለበት ወይም ከደማስቆ በር ወደ ሲሎም የሚወርደውን ቬሌኮርድ (ዛሬ የኤል ዋድ ጐዳናን አቋርጦ የሚያልፈው ሲሆን) መጨረሻው ሰፊ ከሆነ ደርብ የተሠራ ነው ። ሁለተኛ ከዚህ ደረጃ በፊት በውስጡ ትልቅ ማለፊያ ያለው የኢዱሽያ ግድግዳ ክፍል ቆሞ ነበር ።

እቴጌ ኢዱሽያ የደቡባዊውን ከተማ ግድግዳ ሠርተው በነበሩበት ጊዜ በ450 ዓ.ም. አካባቢ የጽዮን ተራራና ሲሎምን በዋናው ከተማ ውስጥ አመጡት የጥንቱ ግድግዳ ከጥቅም ውጭ ነው (ምናልባት በቆስጠንጢኖስ) በመጨረሻ የኤርምያስ ጉድጓድ የነበረው ልክ ከጥንቱ ታላቅ በር ቀጥሎ ነበር ። በተጨማሪ ጉድጓዱ ይልቁንም አንድ ሰፊ የሆነ የካርድ ቫሌንሲስ ክፍል ተገኝቷል ።በትንሽ ክፍል አጠገብ ነበር ።

የምዕራቡ ሰገነት በሦስት ወጋግራዎች ይገለጻል ።ሰገነቱም በሚቀጥለው ማለፊያ ላይ ለጥ ያለ ነው ። የምሥራቁ ወጋግራ በማዳባ ሥዕል ወይም ካርታ ሊታይ ችሏል ። በደቡባዊው የካርድ መጨረሻ ሥዕሉ (ካርታው) የመካከለኛውን ቀዳዳ ቅርጽ ያሳያል ።

እስከ ዛሬ ድረስ እንቆቅልሽ ሆኖ ሲኖር አሁን የኤርምያስ ጉድጓድ መሆኑ ተገልጾ አንድ ለከዋክብት ጥናትና ምርምር የሚያገለግል ቴሌክስኮፕና መስታወት ቅርጽ ያለው ሲምቦል ከአሮጌው ከተማ ግድግዳ በር ላይ እንዳለ የፒያጩንሳ ተሳላሚ ገልጿል ። በኢየሩሳሌም ታሪክ የኮሚያድ ሐረገ መንግሥት መቆረጥና የዕድገቱ ፍጻሜ መሆን የስምንተኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ምስክር ነው ። ከዚያ በኋላ የከተማው ስፋትና ልዕልና እ

ወደ ፲፱ኛው ገጽ ዞሯል

www.ethiopianorthodox.org

# የሃይማኖት ዐምድ

> «ዓለሞች ሁሉ በእግዚአብሔር ቃል እንደ ተዘጋጁ ፣ ስለዚህም የሚታየው ነገር ከሚታዩት እንዳልሆነ በእምነት እናስተውላለን» (ዕብ. ፲፩፥፫) ።

## ምሥጢረ ክህነት

በልሳነ ግዕዝ "ተክህነ" የሚለው የግሥ ቃል ትርጉሙ አገለገለ ማለት ነው ። ክህነት የሚለው ስም ከዚሁ ግሥ የወጣ ስለሆነ ፍችው አገልግሎት ይሆናል ። ከዚሁ ስምና ግሥ የሚወረሠው "ካህን" የተባለውን የቅጽል ስም አገልጋይ የሚል ትርጉም አለው።

ግን ምን አይነት አገልግሎት? የሚያሰኝ ጥያቄ ቢኖር ትርጉሙ በዓለማዊ ኅብረተሰብ መሐል በተለይም ባለፈው ሥርዓተ ማኅበር ድኃው ችግረኛ እንደ አሽከር ወይም ሎሌ ሆኖ ሀብታሞችን እንደሚያገለግል ዓይነት አለመሆኑ መታወቅ አለበት ። ስለዚህም የካህናት አገልግሎት ሰውን ወደ እግዚአብሔር ማቅረብ በመሆኑ በጸጋ እግዚአብሔር ከማሠርና ከመፍታት ሥልጣን ጋር የተያያዘ ልዩ ስጦታ ነው ።

ለዚህም ማስረጃ በኦሪት ዘፀአ 19፡5-6 "ትእዛዙን በእውነት ብትሰሙ ቃል ኪዳኔንም ብትጠብቁ ምድር በመላዋ የኔ ስለሆነች ከአሕዛብ መካከል የተመረጠ ርስት ትሆኑልኛላችሁ ከዚዚም ጋር የተቀደሰ ሕዝብ የካህናትም መንግሥት ትሆኑልኛላችሁ"ተብሎተ ጽፏል ። ይኸውም ካህናት የእግዚአብሔር መንግሥት ተቀዳሚ ባለሟሎችና አገልጋዮች መሆናቸውን የሚያስገነዝብ ነው ።

ዳሩ ግን ይህ ታላቅ ሥልጣን ክህነት በስመ ካህን እንዲሁ የሚዘረፍ የሚወረስ) ሳይሆን በብዙ ነገር ተፈትኖ እንደ ወርቅ ነጥሮ መውጣትን እንደሚጠይቅ በትንቢተ ሚልክያስ ተጽፎዋል።ይኸውም "እርሱ እግዚአብሔር የሌዊን ልጆች ማለትም ካህናት እንደወርቅና ብር ያነጥራቸዋል።እነርሱም ለእግዚአብሔር በጽድቅ ንጹሕ ቁርባንን የሚያቀርቡ ይሆናሉ የሚል ነው ።/ሚል 3፡3- በተለይም ለዚህ አገልግሎት የክብር ጥሪ የደረሳቸውና የሚደርሳቸው ካህናት በሃይማኖት ትምህርት የበሰሉ ለቆሙለት ዓላማ የማያወላውሉ በመልካም ሥነ ምግባር ክርስቶስን የሚወክሉ እንደራሴዎች ለመሆን የበቁ የነቁ ሆነው መገኘት ይገባቸዋል ። ከዚህ ውጭ ያለምንም በቂ ትምህርት በልማድና በዘር የተወረሰ ሥልጣነ ካህናት አለን፣ ሁሉ በእጃችን ሁሉ በደጃችን ማዕረጋችን ምጡቅ አእምሮዋችን ረቂቅ በማለት በግብዝነት የሚምነሸነሹትን የስም ካህናት የእግዚአብሔር ጸጋ አያድርባቸውም ።

ስለዚህም በትንቢተ ሆሴዕ የተጻፈ አስፈሪ ቃል አለ ፣ እርሱም "አንተ ካህኑ ዕውቀትን ከመጥላትህ የተነሣ ሕዝቢ በዕውቀት ማጣት ጠፍቶዋል ስለዚህ ካህን እንድትሆነኝ አልፈልግም ።ምክንያቱም የኔ የአምላክህን ሕግና ትእዛዝ ረስተሃል እኔ ደግሞ ልጆችህን እረሣለሁ እንደብዛታቸው መጠን በደል ሠሩብኝ እኔ ደግሞ ክብራቸውን ወደ ነውር እለውጠዋለሁ" የሚል ነው ሆሴዕ 4፡6-7

በትንቢተ ሕዝቅኤል 34፡1-12 ኃላፊነት የማይሰማቸውንና ለግል ጥቅም ብቻ በመስገብገብ የተበታተኑትን የእግዚአብሔር ወገኖች ከማሰባሰብ ቸል ብለው በግድየለሽነት የሚኖሩ ካህናትን በሰነፎች እረኞች ምዕመናንን በበጎች መስሎ የፈጸሙትን በደል ከዘረዘረ በኋላ " እነሆ እኔ ራሴ በጎቼን ከእጃቸው እፈልጋለሁ፣በጎቼንም ከማሠማራት አስተዋቸዋለሁ በጎቼንም ከአፋቸው አድናለሁ በማለት ኃላፊነት የማይሰማቸውን ካህናት ለምንም የማይፈልጋቸው መሆኑን በግልጽ አስረድቷል ።

ክርስቶስም ይህኑ ምሳሌ በቀጥታ ወስዶ በዮሐ 10፡1-18 እንደተጻፈ ሲናገር ምዕመናንን በመምከርና በማስተማር ወደ እግዚአብሔር ማቅረብን ትተው "እነጋገሩ ባሕታይ አወሳሰዱ እንደዓባይ" እንዲሉ የግል ጥቅማቸውን ብቻ የሚመለከቱ ካህናትን ከእኔ በፊት የሚመጡ ሌቦችና ወንበዴዎች ናቸው በማለት አጋልጧቸዋል ።

ሐዋርያው ጴጥሮስም ይህኑ በመከተል ሲጽፍ ለመንጋው መልካም ምሳሌ ሁኑላቸው እንጂ / ገና በገና የመፍታትና የማሠር ሥልጣን አለን ብላችሁ ማኅበረ ምዕመናኖቻችሁን በኃይል ለመግዛት አትሞክሩ" ካለ በኋላ በዚህ ምክር ተምራችሁ በሥነ ሥርዓት ምዕመናንን ብትመሩ ግን "የእረኞች አለቃ ክርስቶስ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን የክብር አክሊል ትወርሳላችሁ" ሲል አብሥሮአል ።

ስለዚህም ሐዋርያው ጳውሎስ እንደተናገረ "በክህነት ማገልገልን የመረጠ ካህን (ቄስ) የማይነቀፍ የአንዲት ሚስት ባል ልከኛ ራሱን የሚገዛ እንደሚገባው የሚሠራ እንግዳ ተቀባይ ለማስተማር ብቃት ያለው የማይሰክር ጭቅጭቀኛ ያልሆነ ገርነት ያለው በከንቱ የማይከራከር ለገንዘብ የማይስገበገብ ልጆቹን በጭምትነት ሠርቶ ቀጥቶ ማስተዳደር የሚችል የራሱን ቤት በመልካም ይዞታ ማስተማርና ቤተሰቡን መምራት የሚችል መሆን አለበት ። የራሱን ቤት ማስተዳደር የማይችል ከሆነማ የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን እንዴት ማስተዳደር ይችላል ? በትዕቢትም ተወጥሮ በዲያብሎስ ፍርድ እንዳይወድቅ ከአዲስ አማኞች መካከል በችኮላ መሾም አይገባውም ። 1ጢሞ 3፡1-7

ይቀጥላል

ቄስ መክብብ አጥናው



# ፍልሰተ ዓፅሙ ለተክለ ሃይማኖት

የጻድቁ የአቡነ ተክለ ሃይማኖት እናት አባታቸው ጸጋ ዘአብና እግዚእ ኀረያ ይባላሉ ።

እነሱም ልጅ የሌላቸው መካኖች ስለነበሩ እግዚአብሔር ልጅ ይሰጣቸው ዘንድ በጾም በጸሎት ይለምኑ ነበር ። እግዚአብሔርም ጸሎታቸውን ሰምቶ የተባረከ ልጅ አቡነ ተክለ ሃይማኖትን ሰጣቸው ። አቡነ ተክለ ሃይማኖትም ካደጉ በኋላ 25 ዓመት ሲሆናቸው እየተዘዋወሩ በቡልጋና በምንጃር በሸንኮራም ያስተምሩ ጀመር። ከዚያም አልፈው የጉራጌን አገር እያስተማሩ ፣ ወደ ወላይታ ወረዱ ይኸውም ወላሞ ይባል የነበረው አገር ነው ። ያን ጊዜ ግን ይባል የነበረው ሀገረ ዳሞት ነው ። ያን ጊዜ በወላይታ የነበረው አገረ ገዢ ሞተለሚ ይባል ነበር ። እሳቸውም ሞተሎሚን መክረው አስተምረው አሳምነው አጠመቁት ከመጠመቁም በፊት ወደ እግዚአብሔር ጸልየው ልጁ ሞቶበት ሳለ ልጁን ከመቃብር አሥነሥተውለታል። ከዚያም 12 ዓመት ከተቀመጡ በኋላ ተመልሰው ወደ አማራው አገር መጡ።ከዚያም አልፈው ወሎ ውስጥ አማራ ሳይንት ሄደው ከአባ በጸሎተ ሚካኤል ገዳም ጋስጫ ገብተው 10 ዓመት ረድተዋል ። ከዚያም አልፈው ወሎ ውስጥ ሐይቅ ተሁለደሬ ከሚባለው አውራጃ/ወረዳ ከአባ ኢየሱስ ምዓ ገዳም ገብተው እንደዚሁ 13 ዓመት ሲረዱ ኖረዋል ።

ከዚያም ተነሥተው ወደ ትግራይ ሄደው ከአቡነ አረጋዊ ገዳም ደብረ ዳሞ ገብተው ከረዱ በኋላ ከአባ ዮሐኒ ዘንድ መዓርገ ምንኩስና ተቀበሉ ። ከዚያም 12 ዓመት ያህል ከቆዩ በኋላ ወደ ኢየሩሳሌም ሊሄዱ ተነሥተዋል ። ከዚያም ሄደው ፀዓዳ አምባ ከሚባለው ገዳም ገብተው ሐማሴኖች አምባ ሥላሴ ከሚሉት ደረሱ ። ከዚያም በጣም ያረጁና የደቀቁ ሰውነታቸውም በእርጅና የተሠባበሩ አረጋውያን አበውን አግኝተዋል። እሳቸውም ከእነርሱ ተባርከው ተክለ ሃይማኖትም ባርከዋቸው ተቀምጠው ሳለ ከዚህ በኋላ መነኩሳቱም አቡነ ተክለ ሃይማኖት ወደ ኢየሩሳሌም ሊሄዱ ሲነሡ አባ ቀልጠፍ ብለህ በቶሎ ተመለስ ብለው ለመኗቸው ። ከዚያም ተነሥተው የኤርትራን ባሕር ተሻግረው ሄደዋል ጥንት ኤርትራ በዓረብኛ ባሕረ ሱፍ በአማርኛ ቀይ ባሕር በእንግሊዘኛ ሬድ ሲ ይባል ነበር ። ዛሬም ይባላል ። የኤርትራን ባሕር ተሻግረው ኢየሩሳሌም ወርደዋል ። ከዚያም በኋላ ጌታ የተወለደበት ቤተልሔምን የተጠመቀበትን ዮርዳኖስን የተሰቀለበትን ቀራንዮን የተቀበረበትን ጎልጎታን ፣ ይህን የመሳሰሉትን ጌታ ያስተማረበትንና ታምራት ያደረገበትን ቦታዎች ጐብኝተው ወደ ግብፅ ወርደው ካይሮን እስክንድርያን ጐብኝተዋል ። ያን ጊዜ የነበረው ፓትርያርኩ አባ ሚካኤል የሚባለው ነበረ ። ወይም አባ ብንያሚ ይባል ነበር ። አቡነ ተክለ ሃይማኖትም ከእሱ ዘንድ በካይሮ ለመቀመጥና ለመኖር ቢያምራቸውም ፓትርያርኩም ወደ አገርህ ሂድ ክፍልህ ኢትዮጵያ ናትና አላቸው ። ከዚያ በኋላ ከግብፅ ማለት ከካይሮ ተነሥተው ተመልሰው ወደ አገራቸው ወደ ኢትዮጵያ መጥተዋል።መጥተውም ምድረ ግራርያ የሚባለውን እያስተማሩ ለገዳምነት መርጠውታል።ከዚያም ሆነው/ ተቀምጠው/ እያስተማሩ በጸሎት በስግደት ፣ በልዩ ልዩ ሥራና ትሩፋት ተወስነው ሳሉ ብዙ ደቀ መዛሙርት አውጥተዋል አፍርተዋል ከእነሱም አንዱ አቡነ ፊሊጶስ ናቸው ። 12ቱን ንቡራነ ዕድ ሁሉ ያገኙ ከዚሁ ገዳም ነውና።የአቡነ ፊሊጶስ አገራቸው ሰላሌ ውስጥ ሐሮ ከሚባለው ሥፍራ ነው። እነዚህም ብፁዓን አባቶች ኢትዮጵያን እንደ ከዋክብት በወንጌል ትምህርት ያበሩና ያስጌጡ መምህራን (እጨጌዎች) ናቸው።ይኸም ገዳም ታችኛው ገዳመ ኮራ፣ላይኛው ደብረ አሰቦ(ገዳመ ዓሰቦ) እየተባለ እስከ አፄ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት ድረስ ከቆዩ በኋላ በአፄ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመን 1435 ዓ.ም. ገዳም ደብረ ሊባኖስ ተብሎ ተሠየመ ይባላል ። ይሁን እንጂ ወደ ርእሳችን እንመለሳለና ። ለአቡነ ተክለ ሃይማኖት መታሰቢያ በዓመት ውስጥ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የምታከብራቸው 3 በዓላት አሉ ። እነዚሁም 1ኛ ታህሣሥ 24 ቀን በ1197 ዓ.ም. የተወለዱበት ነው ።2ኛ/ ነሐሴ 24ቀን በ1296 ዓ.ም. ያረፉበት ነው ።3ኛ/ ፍልሰተ ዓፅማቸው በ1357 ዓ.ም. ግንቦት 12ቀን ነው ።

ይህንንም አንዳንድ ታሪክ ጸሐፊዎች በመቃወምና ባለመስማማት የተወለዱበትን በ1152 ዓ.ም. ይላሉ ። ያረፉበትን ደግሞ በ1266 ሲሉ ፍልሰተ ዓፅማቸውንም በ1353 ይላሉ ይህንን በዘመናችን ያሉት የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ተከራክረው ውሳኔ ቢሰጡበት ከክርክር ለመዳን ይቻላል ።

ስለ ፍልሰተ ዓፅማቸው ገድሉ እንደሚለው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በራዕይ አሁን ካለበት ቦታ የሚቀበር መሆኑን ለተክለ ሃይማኖት ነግሯቸው ነበር። ልክ በተቀበሩ በ57 ዓመት በእጨጌ ሕዝቅያስ ዘመን 12ቱ ንቡራነ ዕድ የመንፈስ ቅዱስ ልጆቻቸው ከየሀገረ ስብከታቸው ተሰብስበው መጥተው ግንቦት 12 ቀን ዓፅማቸውን አፍልሰው አውጥተው ጌታ እንደተናገረው አሁን ካለበት ቦታ ቀብረዋቸዋል ። መጀመሪያ የተቀበሩት ደብረ ዓስቦ ሲሆን ዓፅማቸው የፈለሰው ከደብረ ዓሰቦ ወደ ደብረ ዓለም ነው ። ዓለምም የሚባለው አሁን ደብረ ሊባኖስ እየተባለ የሚጠራው ነው ። የአቡነ ተክለ ሃይማኖት በየዓመቱ ግንቦት 12 ቀን የሚከበርበት ምክንያቱ ፍልሰተ ዓፅማቸውን ለማሰብና ለማስታወስ ነውና ።

እኛም ከዚህ ዓለም ፈልሰን በሞት ተለይተን ከመሔዳችን አስቀድሞ በዚህ በምድራዊ ዓለማችን ሳለን ንስሐ ገብተን ከኃጢአት ርቀን ለጽድቅ የሚያበቃ ሥራ ሠርተን ተዘጋጅታችሁ ኑሩ ብሎ ጌታችን እንዳስጠነቀቀን ሁሉ ዕድሜ ለንስሐ ዘመን ለፍስሐ እንዲሰጠን እንለምነው ።

አባ ቸርነት ጋሻው በዛ



www.ethiopianorthodox.org

# የመቃብር ሐውልት ጥቅሙ ምንድን ነው?

በሙታን መቃብር ላይ ቤት ወይም የመቃብር ድንጋይ ሐውልት መስራት መች እንደተጀመረ ማን እንደጀመረው በየትስ አገር እንደተጀመረ አይታወቅም ።

ይሁን እንጂ ስለ ጥንት ሕብረተሰብ የኑሮ ሁኔታ የሚናገሩ አንዳንድ አዋቂዎች የመቃብር ሐውልት ሥራ የተጀመረው የሰው ልጅ ድንጋይ የሚጠርብበትን ና እንጨት የሚቆርጥበት መሣሪያ ካገኘ ወዲህ ነው የሚል አስተያየት ይሰጣሉ።በሌላ በኩል ደግሞ ከክርስቶስ ልደት በፊት በአምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ግሪካውያን ሬሳ ያቃጥሉና አመዱን ሰብስበው ቤት ሠርተው ለመታሰቢያነት ያኖሩት ነበር ይባላል እንዲሁም ሮማውያን ሬሳን ቀብሮ መቃብር ቤት መሥራት እንደጀመሩ የሚተርክ ታሪክ አለ የአውግስቶስ አድርያን መቃብር እንደ ማስረጃነት ይቆጠራል የተጀመረውም ሟቹ ትልቅ ሰው እንደ ነበር ለማሳወቅ ተብሎ ነው ይባላል።

ከዚያ በኋላ ግን ጥቂት በጥቂት እያለ ነገሩ ተለመደና ጀግኖች ታላላቅ ሰዎች አውሬ የገደሉ አዳኞች ሲሞቱ መቃብር ቤት ይሰራላቸው ጀመር ከጊዜ በኋላ ግን መቃብር ቤት እየተሻሻለ በሙታን መቃብር ላይ በእብነ በረድ ሐውልት መሥራት ተጀመረ ። ይህም ድርጊት ስለተለመደ ሰዎች ይጠቀሙበት ጀመር ።

ወደ ሀገራችን መለስ ብለን የተመለከትን እንደሆነ ደግሞ ለሙታን መቃብር ቤት መስራት ከተጀመረ ብዙ ዘመናት አልፈዋል የሚሰራውም መቃብር ቤት ለቤተ ክርስቲያን ና ለሕብረተሰቡ ብዙ ጥቅም ሲሰጥ እንደኖረ የሚከተለውን እናቀርባለን ።

ሀ - የዜማ መምህራን፣ የቅኔ መምህራን የንባብ መምህራን ለሙታን በተሰራው መቃብር ቤት እየኖሩ የሕብረተሰቡን ልጆች እያስተማሩ ለሀገር ሲያበረክቱና ቤተ ክርስቲያንንም ሲያገለግሉ ኖረዋል

ለ - ጧሪና ቀባሪ ያጡ ሽማግሌዎችና አሮጊቶችም በመቃብር ቤት እየኖሩ በቤተ ክርስቲያን እየተረዱ ኑረዋል ሻሬም አሉ ።

ሐ - የዓለምን ጣዕም ንቀው የመነኑ ደጋግ ሰዎችም በጾምና በጸሎት ተወስነው ለራሳቸው ለሐገርም እያዘኑ እየጸለዩ የሚኖሩ በመቃብር ቤት ነበር።

መ - የሰንበቴና የማኅበር መዘከሪያ እየሆነ ብዙ ሰዎች እየተሰበሰቡ ሲረዳዱበት ቆይተዋል በሰላምና በፍቅር ጸንተው ወንድማማች እየሆኑ ኖረውበታል።

ሠ - ዕቃ ቤት ይሆንና ንዋየ ቅዱሳት ይቀመጥበታል የቤተ ክርስቲያን ቅርስ ማኖሪያ ይሆናል ።

\- በፍልሰታም ሆነ ሌሊት አገልግሎት በሚሰጡበት ጊዜ ሁሉ የካሕናት ማደሪያ ይሆናል በዚህ ብቻ ሳይወሰን ከሩቅ የመጡና የመሸባቸው እንግዶች ያድሩበታል አርፈው ይሰነብቱበታል በቅጽረ ቤተ ክርስቲያንም ሆነ በአካባቢው ለሙታን የተሠራ መቃብር ቤት ለቤተ ክርስቲያንና ለሕብረተሰቡ በዚህ መንገድ ይህንን የመሰለ መልካም ጥቅም እየሰጠ እያሌ ዘመናትን አሳልፏል ። ይህንንም አጉልቶ የሚያሳየው የመሐይምነት ዘመቻ በተጀመረበት ወቅት እንኳን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የመሰረተ ትምህርት መማሪያ እንዲሆኑ ያቀረበቻቸው በቅጽሯም ውስጥ ሆነ በአካባቢዋ የሚገኙትን የመቃብር ቤቶች ስለሆኑ ሰፋ ያለ ጥቅም በመስጠት ላይ ይገኛል ።

የመቃብር ሐውልት ሥራስ ወደ ሐገራችን ወደ ኢትዮጵያ የገባው በምን ጊዜ ነው?የሚል ጥያቄ ይቀርብ ይሆናል።ዘመኑ ተለይቶ ባይታወቅም ጠላት ከመግባቱ በፊት በነበረው ዘመን በአዲስ አበባ በደሴ፣ በድሬዳዋ ከተማዎች የሚኖሩና ለንግድ የመጡ የውጭ ሀገር ዜጎች ለሞቱት ዘመዶቻቸው መታሰቢያ ይሆን ዘንድ በመቃብራቸው ላይ ሐውልት ያሰሩ ነበር ይህም አነስተኛ በመሆኑ እንደብርቅና እንደ ድንቅ ነገር ሆኖ ሲታይ እንደነበር በዘመኑ የነበሩት ሰዎች ይናገራሉ ጠላት ድል ሆኖ ከሀገራችን ከወጣ በኋላ ግን በስደት ምክንያት በልዩ ልዩ ክፍለ ዓለማት የነበሩ ፣ በትምህርት በሥራ ፣ በሹመት ምክንያት ውጭ ሀገር የቆዩ ኢትዮጵያውያን ካመጡት ከውጭ ሀገር ባሕል መካከል አንደኛው የመቃብር ሐውልት እንደነበር ይነገራል ።

ይህም በመሆኑ እየዋለ እያደረ የመቃብር ቤት መስራት እየቀነሰ በሙታን መቃብር ላይ የሐውልት ሥራ እየተለመደ ሄደ የሐውልቱም ዕብነ በረድ የሚመጣው ከኢጣልያንና ከግሪክ በመሆኑ ከፍያለ ወጪ ይጠይቅ ነበር ፎቶግራፉም እየተሰራ የሚመጣው ከዚያው አገር ነው አሠሪው እንደመረጠው የመነሻው ዋጋ አስር ሺህ ሲሆን የመጨረሻው ግን እስከ ሃያ ሺህ ብር ይደርስ እንደ ነበር አንዳንድ አሠሪዎች ይናገራሉ። አሰሪው ሀብት ካለው ከዚህም በላይ ከፍሎ ለማሰራት ይችላል የዕብነበረዱ ድንጋይ ልዩ ልዩ መልክ ቢኖረውም በአሰሪዎች ዘንድ ተወዳጅነትና ከፍ ያለ ዋጋም ነጭ መልክ ያለው የእብነ በረድ ድንጋይ እንደሆነ የታወቀ ነው ይህም ከለውጡ በፊት የነበረው ሁኔታ ነው ።

ከለውጡ ወዲህ ደግሞ የእብነ በረድ ድንጋይ ከውጭ ሀገር መምጣቱ ቀርቶ የሚመጣው ከሐረርና ከትግራይ ነው መልኩም አንደኛ ዳልቻ ሁለተኛ ጥቁር ነው ከመቃብር ሐውልት ሥራ ክፍል ጠይቀን እንደተረዳነው አሠሪው እንደመረጠው የመነሻ ዋጋ 1200 ብር (አንድ ሽህ ሁለት መቶ ብር )ሲሆን የመጨረሻው ደግሞ 3000 ብር ሶስት ሺ ብር ነው ይህ ሐውልት ስራዎችን የሚመለከት ሲሆን ፎቶ ግራፉን ለመለጠፍ የተለየ ድርጅት አለ ። ከሱም ጠይቀን እንደተረዳነው የሟቹን ፎቶ ግራፍ ከወሰደ በኋላ እንደሚገባው አድርገው አሳድገው በእብነ በረዱ ላይ ለመለጠፍ መነሻው ዋጋ 75 ብር ሰባ አምስት ሲሆን እየሰፋና እየጨመረ በሄደ ቁጥር ዋጋውም እስከ 350 (ሦስት መቶ ሃምሳ ብር ) እንደሚደርስ ተነግሮአል ፊደሉን በዕብነ በረዱ ላይ ለመጻፍ ደግሞ በአንድ ፊደል ሰማንያ ሳንቲም ይከፈላል ይህም ሲባል የዋጋውን ዝርዝር ለማስታወቅ ሳይሆን ይህ ሁሉ ገንዘብ ወጪ ሆኖ ተሰርቶና የብዙ ሰራተኞች ጉልበት ፈሶበት የተሰራው የመቃብር ሐውልት እንክብካቤ ጎሎት ንጽሕና አጥቶ ተጎሳቅሎ ሲታይ የሚያሳዝን መሆኑን ለመግለፅ ነው።

እንግዲህ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በሚገኙት አድባራትና ገዳማት በምንዘዋወርበት ጊዜ እያሌ የሆኑ የመቃብር ሐውልቶችን እናያለን የቤተ ክርስቲያን ተከታይ የሆነ አማኝ ሁሉ በሕይወተ ሥጋ ሳለ በተቻለው መጠን ከሚያደርገው እርዳታ በላይ ወዳጅ ዘመዱ ሲሞትበት አዝኖና አልቅሶ ለሙታን የሚደረገውን ሥነ ሥርዓት ፈጽሞ የሞተውን ዘመዱን ወደ ዘላለም እረፍቱ በክብር ይሸኘዋል የሞተውን ዘመዱን ከቀበረ በኋላ ከዚያው ጥሎ አይረሳውም ለሙቱ መታበቢያ የሚሆነውን ሐውልት በመቃብሩ ላይ ያሰራለታል የተመልካችን ዓይንና ልብ የሚስቡ ጽሑፎችን በማስፈር በሚያውቁት ሆነ በማያውቁት ዘንድ እንዲታወስ ያደርጉታል ።

ስለዚህ በአጠቃላይ የተመለከትን እንደሆነ ሰው በአርአያ ሥላሴ የተፈጠረና ዓለምን እንዲያስተዳድር የተፈቀደለት እንደመሆኑ መጠን እንኳን ሙቶ በሕይወቱም ሳይቀር ክብርና መታሰቢያ ሊደረግለት የሚገባ ነው። ስለዚህም መዝሙረኛው ዳዊት በመዝሙር 111 በቁጥር 6 ለዘላለም አይናወጥም የጻድቅም መታሰቢያ ለዘላለም ይኖራል » ሲል ተናግሮአል ይህም አነጋገር መልካም የሰሩ ሰዎች ሁሉ ለስማቸው መጠሪያ የሚሆን መታሰቢያ ቢቆምላቸው ጠቃሚ መሆኑን ያመለክተናል ።

ይሁን እንጂ ለሙታን መታሰቢያ የሚሆን ሐውልት ይሰራል ቢባልም የመልካም ሰው ስም በሥራው ከመቃብር በላይ ሲጠራ መኖሩ ግልፅ ነው ነገሩ ይህ ሆኖ ሳለ የሙቱን ስም በመጠነኛ ሐውልት በእብነ በረድ ለመቅረጽ የሚያደርጉት ድርጊት ለብዙ በጎ ሥራዎች ሊውል የሚችለው ገንዘብ በከንቱ ባክኗል ብንል ከውነት አንርቅም ለዚህም ምስክር በየደብሩ ሊባኖስና በየከተማዎቹ በሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት ቅጥር ግቢ ውስጥ ቆመው የሚታዩትን ሐውልቶች መቃኘት ይቻላል እኛ የምንለው ሐውልቱን ለምን ሠሩ ሳይሆን ብዙዎቹ ሰዎች ለሞቱት ዘመዶቻቸው ብዙ ገንዘብ ከፍለው ሐውልት ማስራታቸውን እንጂ ሐውልቶቹ በልዩ ልዩ አጋጣሚ የተነሳ እንዳይበላሹ መጠበቁንና መንከባከቡን ጨርሰው አያስቡትም እንዲያውም ከሰሩ በኋላ ብዙ ሺህ ብር የፈሰሰ በትን መቃብር ለመመልከት አይፈልጉም ።

ይህ ብቻ አይደለም ሐውልቶችን በሚመለከት ብዙ ችግሮችን ለመዘርዘር ቢቻልም እዚህ ላይ በተለይ ልንጠቅሰው የምንወደው በየጊዜው የሐውልቶች ቁሳቁሶች በሌቦች መሰረቅ ነው ። ይህም ሊሆን የቻለው በየሥፍራው እንደምንመለከተው የመቃብር ሥፍራዎች በአጥር ያልታጠሩ፣ንጽህናቸው ያልተጠበቀ፣ ሥነ ሥርዓትን የሚያስከብሩ ዘበኞች ስላልተቀጠሩላቸው የማንም መተላለፊያ የሆነው ይገኛሉ ።

ይህም በመሆኑ ብዙ ሀብት የፈሰሰበት የመቃብር ሐውልት በሌቦች እየተሰበረ የሥዕሎቹ ፍሬሞች የአበባ ጉንጉኖችንና ሰይፍ የያዙ መላእክት የተሳሉባቸው ፡ የእብነ በረድ ከፈፎች የማገር ድንጋዮች የአጥሩ ብረቶች እየተሰባበሩ ፣ እየተነቃቀሉ ይወሰዳሉ ብዙ ዋጋ ወጥቶ የተሰራውንም ዕቃ ወስደው ለቀላል ዋጋ እንደሚሸጡት ይነገራል ።

ይህ ብቻ አይደለም ሀውልቱ ጠባቂ ከማጣቱ የተነሳ ልጆች ከአንዱ ሐውልት ወደ አንዱ ሐውልት እየዘለሉ ሲጫወቱ በድንጋይም እየወረወሩ እንደሚሰብሩት የታወቀ ነው ይህ እንዳይሆን የሙታን ዘመዶችና የቤተ ክርስቲያን ባለሥልጣኖች ተወያይተው ዘበኛ እንዲቀጠር ንጽሕናው እንዲጠበቅ ቢያደርጉ ይህ ሁሉ ችግር ሊታረም ይችል ነበር እንዲያውም ለሙታን የመታሰቢያ ሐውልት ከተሠራ ዙሪያውን አበባ ተተክሎ ውኃ እየጠጣ በንጽሕና ቢያዝ ሰዎችን ስለሚስብ መናፈሻ መሆን ይችላል ይህ ከሆነ የሙታንን ከተማ ብዙ ሰዎች ሊጎበኙት ይወዳሉ ።

በአሁኑ ይዞታ ከቀጠለ ግን የመቃብር ሐውልቶች ያሉበት ሥፍራ ሁሉ ንጽህና ስለጎደለው ለሰው ተላላፊ በሽታን ሊያመጣ ከመቻሉም ሌላ የቤተ ክርስቲያንም መልክና ይዞታ ከማበላሸት አልፎ ወደ አስቀያሚነት ደረጃ ደርሶአል እንግዲህ የሚሠራውን ሐውልት ሌባ እያፈረሰ የሚወስደው ከሆነ ለሐውልት መስሪያ የሚወጣው ገንዘብ ሌቦች ወደማይሰርቁት ወደ እግዚአብሔር መዝገብ እየተሰበሰበ ጧሪ ቀባሪ አጥተው በየቤተ ክርስቲያኑ ወድቀው ለሚገኙት አሮጊቶችና ሽማግሌዎች ቢጦሩበት ወላጅ የሌላቸው ሕጻናት እየተማሩ ቢአድጉበት ለሞቱት ሰዎች ከዚህ የበለጠ መታሰቢያ ሊገኝ አይችልም የጻድቅ ሰው መታሰቢያ ለዘለዓለም ይኖራል የሚለው ትርጉሙ ይህ ነውና ።

አለቃ ነቢየ ልዑል ዮሐንስ

## ደብዳቤዎች

ከገጽ ፩ የዞረ

የተዘጋጀው ትምህርት ይሰጣችዋልና ።

እርስዎም ከፈለጉ አንድ የተዘጋጀ ሺት እንደምንም እንፈልግልዎታለንና ወደ ድርጅታችን ብቅ ይበሉ ።

6ኛ፣ የመጽሔታችንና የጋዜጣችን ደምበኛ ለመሆን የሚከተለውን አሟልተው ከላኩልን በየጊዜው ሊደርስዎ ይችላል ።

| | | |
|---|---|---|
| ሀ ለመጽሔት የዓመቱ | | |
| ክፍያ ብር | 6.00 | |
| ለ የፖስታ አገልግሎት | 1.80 | ለአ.አ |
| ሐ ለጋዜጣ የዓመቱ | 2.40 | |
| መ የፖስታ | 3.60 | ለአ.አ |
| ድምር | 13.80 | |

ወደ ፳፱ ገጽ ዞሯል





www.ethiopianorthodox.org

# «ክርስቲያኖች ለአዲሱ ሕብረተ ሰብ»

በዓለም ክርስቲያን ተማሪዎች ፌዴሬሽን የአፍሪካው ክፍል ጽ ቤት አዘጋጅነት ፦« ክርስቲያኖች ለአዲስ ሕብረተ ሰብ » በሚል ዐቢይ ርእስ ሰባት ቀን የፈጀ የጥናት ጉባኤ በኬንያ ዋና ከተማ ናይሮቢ ውስጥ ከየካቲት 12 - 24 ቀን 73 ዓ.ም ተካሂዷል ። የጥናት ጉባኤው የተደረገው በመላው አፍሪካ አብያተ ክርስቲያናት ኮንፈረንስ የማሠልጠኛ ማዕከል ውስጥ ነው ። በመሆኑም የዚሁ የኤ.ኤ.ሲ.ሲ. የማሠልጠኛ ማዕከል በመስተንግዶ ከፍተኛ ተሳትፎ አድርጎአል ።

በዚሁ የጥናት ጉባኤ ፡ -የኢትዮጵያ፣ የጋና ፣ የአዛኒያ (ደቡብ አፍሪካ )፣ የዝምባብዌ፣ የማዳጋስካር ፣ የሲዮቶ ፣ የዛየር፣ የላይቤርያና የኬንያ ብሔራዊ የክርስቲያን ተማሪዎች እንቅስቃሴ ተወካዮች ተሳታፊ ሲሆኑ ፣ በጠቅላላው ከሃያ በላይ ተወካዮች ተገኝተዋል ። ከኢትዮጵያ ሃይማኖተ አበው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበርን በመወከል ሁለት አባሎች ጉባኤውን ተሳትፈው ተመልሰዋል ።

ጉባኤው በተካሄደበት ወቅት ተሳታፊዎች የየሀገራቸውን የክርስቲያን ተማሪዎች እንቅስቃሴ (ኤስ ሲ. ኤም )፣ ቤተ ክርስቲያንና የመንግሥቱን ፖለቲካዊ አቋም በሚመለከት ሰፋ ያለ መግለጫ በየተራ አቅርበዋል ።

ከያንዳንዱ ተወካይ ንግግርና መግለጫ መረዳት እንደተቻለው ፡ አብዮት በሚያካሂዱና ለነፃነት በሚታገሉ ሀገሮች የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት ያሳዩት ተጋድሎና የገጠማቸው ችግር ተዘርዝሮአል። በሌላ በኩል ደግሞ የአብያተ ክርስቲያናት ደካማ ጎን ሳይተችበት አላለፈም ቤተ ክርስቲያን ወንጌልን ተግባራዊ በሆነ መንገድ ለኅብረተሰቡ ባለመስበክዋ ለችግሩ ከተጠያቂነት እንደማትድን ተነግሮአል ። ቤተ ክርስቲያን በኅብረተሰቡ ያለውን የባርነት ኑሮ የብዝበዛ ወንጀልና ኢሰብአዊ የጭቆና አገዛዝ እስከ መስዋዕትነት ድረስ ባለመቃወሟ ነፃነት፣እኩልነት ፍትሕ የሰፈነበት አዲስ ሕብረተሰብን ለመፍጠር በሚደረገው የትግል ሜዳ አለመሰለፍዋን ያረጋግጣል። በመሠረቱ ቤተ ክርስቲያን ከክርስቶስ ትምህርት የተነሣ የኅብረተሰቡ መሪ መሆን ይገባት ነበር ። ቤተ ክርስቲያን ከክርስቶስ የተቀበለችውን የእውነት ቃል ለዓለም በማቅረብ ለሁሉ የምትታይ በተራራ ላይ ያለች የብርሃን ከተማ ነች። ግን አንዳንድ መሪዎቿ ከጠረጴዛ በታች እንደተቀመጠ መብራት በማድረግ ፋናዋን እያጨለሙ ናቸው። ይሁንእንጂ በአንዳንድ የአፍሪካ ሀገሮች ያሉ አብያተ ክርስቲያናት ያለፈ ስሕተታቸውን በመረዳት ንስሐ ገብተው እኩልነት ፍትሕና ሰላም የሰፈነበት ኅብረተሰብ ለመፍጠር ከሚታገሉ ኃይሎችን ተሰልፈዋል። በሌላ በኩል ደግሞ እስካሁንም በክፉው የዓለም መንፈስ በመገፋፋት የተለያየ የፖለቲካ ፓርቲ ፈጥረው ለግል ጥቅምና ለሥልጣን የሚታገሉ የሃይማኖት ክፍሎች አሉ።ዛሬ አብዮት ባካሄዱ የአፍሪካ ሀገሮች ሁሉ ስንመለከት የኅብረተሰቡን አብዮት ቤተ ክርስቲያን በግንባር ቀደምትነት የመራችበት ሀገር አናይም ። ምንም እንኳን ቀሰስ ሲቶሊና አባ አቤል ሙዜሬዋ ለተወሰነ ጊዜ ለኅብረተሰብ ነፃነት ታጋይ የክርስቲያን አርበኛ መስለው ቢታዩ፣ወደ ግል ጥቅማቸው ስላዘነበሉ ከትግግል ሜዳ ወጥተዋል ። የእነዚህ መሪዎች አቋም በአፍሪካዊት ቤተ ክርስቲያን የታሪክ ገጽ ጥቁር ነጥብ ጥሎ አልፎአል ።

ክርስቲያኖች ወንጌልን ተግባራዊ ለማድረግ ቢጥሩ ኖሮ ነጻነትን፣ፍትሕንና እኩልነትን የሚያበስረው ክርስትና በዓለም ላይ ሊሰፍን በቻለ ነበር። ቤተ ክርስቲያን ኅብረተሰቡን ለመገንባት ለተደረገላት ጥሪ የሰጠችው መልስ ይህን ያህል የጎላ አይደለም ። ይሁን እንጂ ሰብአዊ እኩልነትን ፣ ነፃነትን ፣ ፍትሕንና፣ ሰላምን በዓለም ላይ ለማስፈን የታገሉና የሚታገሉ እውነተኞች ክርስቲያን አርበኞች በየሀገሩ መኖራቸው አይካድም ።

ቤተ ክርስቲያን የማይበገር ሰማያዊ ኃይል አላት ። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን ባላት መንፈሳዊ ሰማያዊና ምድራዊ ኃይል ተጠቅማ ኅብረተሰቡን ወደ ነፃነት በመምራት አዲሱን ነፃ ኅብረተሰብ በግብረገብነት መገንባት ይገባታል። ማንኛውም ቅን ሐሳብ በወንጌል ሊጠየቅ ይችላል፣በክርስትናም ሊተች ይችላል ። ክርስቶስን በለበሱ ክርስቲያኖችም ከመተርጎም አያልፍም።ስለዚህ ክርስትና ለመልካም ሥራ ራስን መሥዋዕት እስከ መድረግ የሚያደርስ መመሪያ ነው ። ዛሬ ቤተ ክርስቲያን ማድረግ የሚገባትን በሙሉ ባለማድረጓ በኅብረተሰቡ ዘንድ ልታበረክተው የሚገባትን ተልእኮ አለመፈጸምዋን ያስረዳል ።

የክርስቲያን ተማሪዎች ወጣቶች እንቅስቃሴዎች የቤተ ክርስቲያን አካል ናቸው ። የሚሰጡት አገልግሎት ክርስቲያናዊ ነው፣ እያንዳንዷ ቤተ ክርስቲያን የየሀገርዋን ክርስቲያን ተማሪዎች መንፈሳዊ እንቅስቃሴ የምትረዳው የምትደግፈው እምብዛም ነው ። ስለሆነም ይህን ስንል ፣ በማቴሪያል ድጋፍና የገንዘብ አስተዋጽኦ በማድረግ የሚረዱ አብያተ ክርስቲያን እንዳሉ አንክድም ክርስቲያኖች ለአዲሱ ኅብረተ ሰብእ ስንል በቤተ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ መንፈሳውያን ወጣቶች ከፍተኛ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ ። ክርስቲያኖች ኅብረተሰቡን ወደ ተሻለ ኑሮና ሕይወት መለወጥ አለባቸው ። ነፃነት ፣ እኩልነትና ትክክለኛ ፍትሕ በኅብረተሰቡ መካከል እንዲሰፍን መታገል አለባቸው ። አዎ ይህን ለመፈጸም የሚጠብቀው ተጋድሎ ቀላል አይደለም።ሆኖም ክርስቶስን ያመነ ክርስቲያን፦«እኔን መከተል የሚወድ ቢኖር ራሱን ይካድ መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ» የሚለውን መለኮታዊ ቃል በተግባር ለመቀበል መዘጋጀት ይኖርበታል ። ስለዚህ ኅብረተሰብን ለመገንባት በሚደረገው ትግል የክርስቲያን ተሳትፎ አሁን ካለው ሊያድግና ሊሰፋ ይገባዋል ።

ሴቶች ከባህልና መደብ ጭቆና ነፃ ለመውጣት የሚያደርጉት ትግል ድርብ በመሆኑ በተለይ ሊታሰብ ይገባዋል ። ቤተ ክርስቲያን ከባህልና ከልማድ የተነሣ በሴቶች ላይ ያላት አመለካከት እስከዚህም አልተሻሻለም ። በባህል ተጽእኖ የተነሣ በቤተ ክርስቲያን የሴቶች ተሳትፎ በጣም የተወሰነ ነው ። ይህ ሁኔታ በክርስቲያኑ ማኅበረ ሰብእ ሊቀጥል አይገባውም።ክርስቲያኖች ለአዲሱ ኅብረተሰብእ የተሟላ አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉት በውስጣቸው ያለውን ጉድለት በቅድሚያ ሲያስተካክሉ ብቻ ነው በመሆኑም በሴቶች ላይ የሚደረገው የልማድና የባህል ተጽእኖ የተለየ ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ ሆኗል ። ሰዎች ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት እኩል ናቸው በተግባር ግን ተቃራኒው ቦታውን ይዞ ይታያል ። የዘር መድልዎ ፣ የቀለም ልዩነት፣የጾታ ጭቆና...ወዘተ ገና በኅብረተሰቡ ፈጽሞ አልጠፋም ክርስቲያኖችም እንኳ ከዚህ አለመንጻታቸው ያሳዝናል ። የሴትን ልጅ የሰብእና ክብር ከወንድ ዝቅ አድርገው የሚመለከቱ ገና ብዙዎች ናቸው ። አዲሱ ኅብረተሰብ ከዚህ ዓይነት ወደኋላ ቀር አስተሳሰብ ካልጸዳ ትክክለኛ ፍትሕ ፣ ነፃነትና ሰብአዊ እኩልነት ሊሰፍን አይችልም ። ይህም የትግል እርምጃ ከክርስቲያኑ ማኅበረ-ሰብእ ጀምሮ መቀጠል አለበት ።

ይህ ጉባኤ የየሀገሮቹን ወቅታዊ ሁኔታዎች በማስመልከት ከተወካዮች የተሰጡትን መግለጫዎች ከገመገመ በኋላ ተሳታፊዎችን በሦስት ቡድን በመከፈል ጥናቱን ቀጥሏል ። የጉባኤው ጠቅላላ ሀሳብ በሦስት ዋና ዋና ነጥቦች ተጠቃልሎ በጥያቄ መልክ ከሰፈረ በኋላ ፣ ለእያንዳንዱ ቡድን አንድ ጥያቄ በመስጠት ሰፊ ውይይት ተደርጎባቸዋል ።

ቡድኖቹ በየግላቸው በተሰጣቸው ጥያቄ መሠረት ጠለቅ ያለ ውይይት ካደረጉ በኋላ የውይይቱን ውጤት ለጋራ ጉባኤው አቅርበዋል ።

ጉባኤው የየቡድኑን ሪፖርት በተራ ካዳመጠ በኋላ ሀሳቦችን በመጭመቅ ማጠቃለያ ሰጥቶአል ። ይኸውም ጠቃሚ ነጥቦችን በመልቀም ያልተብራሩትን እንዲብራሩ በማድረግና የመጨረሻ ውይይት በማካሄድ ነው ። --

በማጠቃለያው እንደተገለጸው ቤተ ክርስቲያን ለነጻነት በሚደረገው ትግል አኳያ እስካሁን የሚፈለግባትን ያህል እንዳልፈጸመች ተገምቶአል። ክርስቲያን ተማሪዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያላቸው ድርሻ መጠነኛ ነው ። ሆኖም ወደኋላ ቀር ባህልና አጉል ልማድን ከቤተ ክርስቲያን ሕይወት ለማስወገድ እስካሁን የማይናቅ ትግል አድርገዋል። ክርስቲያን ተማሪዎች ከቤተ ክርስቲያን አካል አንዱ ክፍል ብቻ እንደመሆናቸው መጠን የሚያደርጉት ትግል ምሉዕ ሊሆን አይችልም ። መላዋን ቤተ ክርስቲያን መቀስቀስና በስፋትና በምልዓት ለኅብረተሰቡ የሚያበራ የወንጌል ፋና ማስጨበጥ አለባቸው ። ለዚህም ክርስቲያናዊ ተልእኮው በይበልጥ መቀጠል አለበት ። በዚህ በኩል የዓለም ክርስቲያን ተማሪዎች ፌዴሬሽን ከምን ጊዜውም የበለጠ ኃላፊነት ይጠብቀዋል ።

ከዚህ በኋላ ይህ የጥናት ጉባኤ ። - «ክርስቲያኖች ለአዲሱ ኅብረተሰብ » በሚል ዐቢይ ርዕስ የጀመረውን የሰባት ቀን ስብሰባ ፈጽመዋል። አጠቃላይ የጥናት ጉባኤው ሪፖርትም ለአዘጋጁ ክፍል ለዓለም ክርስቲያን ተማሪዎች ፌዴሬሽን የአፍሪካው ክፍል ጽ ቤት እንዲተላለፍ ተደርጎአል ።

ከኢትዮጵያ ፡ - ጉባኤውን ከተሳተፉ
የሃይማኖት አበው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር ተወካዮች የቀረበ።

## የኤርምያስ ጉድጓድ ...

ከገጽ ፲፫ የዞረ

የቀነሰና እየተበላሸ ሄደ ። የኢዮሺያ ግድግዳም ደረጃ በደረጃ ወይም ቀስበቀስ እየፈራረሰ ወደቀ ። ከኢዮሺያ በፊት የነበረው ወሰን እንደገና በደቡባዊው የከተማ ክልል ተወሰነ እስከ አሁን ድረስም አለ ።

በ985 ዓ.ም የእስላም መኖሪያ የሆነችው ኢየሩሳሌም አልሙከድሲ የከተማውን በሮች ዝርዝር ወይም ሊስት ይሰጠናል ቅድስቲቱ ከተማ ስምንት የብረት በሮች አሏት ።

1/ የጽዮን በር (ወደ ምዕራብ የሚወስደው የአሁኑ ጽዮን በር)
2/ የነያ በር (ከቱህ ደቡባዊ መጨረሻ ይልቅ የካርዶ ማክሲሙስ ጥንታዊ ዘመን ነው ።)
3/ የባላት በር (ምናልባት ለጲላጦስ ወይም ጉዳና ይህም መንገድ ሰፍያንና ቅዱስ ጴጥሮስን በማያያዝ በዚህ በር አልፎ ይሄዳል)
4/ የኤርምያስ ጉድጓድ በር (በአሁኑ ጊዜ የዶንጌት አካባቢ ነው)
5/ የሲሎም በር (ኤልአክሳንና ሴሎምን ያገናኛል)
6/ የኢያሪኮ በር (የቅዱስ እስጢፋኖስ ወይም የአንበሳዎች በር)
7/ የኤልአሙድ በር (የደማስቆ በር)
8/ የማኅበረ ዳውድ በር (የጃፋ በር)

በደቡብ ግድግዳ ያሉት ያምስቱ በሮች ጠቅላላ ሁኔታ በእርግጥ ያስደንቃል ። ጥቅሱ ለአምስቱ ንዑሳን በሮች ብቻ መሆን ይችላል ። በአሥረኛው ክፍለ ዘመን ወደ ደቡብ ኢየሩሳሌም ከሚወስዱት ከተለያዩት መንገዶች በእያንዳንዱ ላይ የቆሙ መሆን አለባቸው ዋናው ትራፊክ በመጨረሻ በተገለጹት ሦስት በሮች ውስጥ ሄዷል ከሌሎችም ንጮች እንደምናውቀው ከመስቀል ጦርነት በፊት የነበረው የቆሳጢንጢኖስ የሕወት ታሪክም እንደዚሁ ነው ወይም ተመሳሳይ ነው በኤርምያስ ጉድጓድ አጠገብ ለቅድስት እሌኒ ጉድጓድ አስም ሷል ወይም ዋሻ አሳፈልፍሏል ። ከመስቀል ጦርነት ዘመን ቀደም ሲል ደግሞ አንድ ሌላ ተሳላሚ ዳንኤል የተባለ እራሻያዊ አበምኔት ከቅዱስ ሰባ ገዳም የኤ

ተከታዩ ወደ ገጽ ፳፬ ዞሯል




www.ethiopianorthodox.org

# የቤተሰብ ዓምድ

አዘጋጅ ንብረት አበበ

በዚህ ዝግጅት የምናስተዋውቃችሁ አባ ጐሹ ተሰማንና ባለቤታቸው እማ ሆይ ፀዳለ ዘወልዱን የ66 ዓመት የጋብቻ ሕይወት በሚመለከት ካሉበት ድረስ ሄደን ላቀረብንላቸው ቃለ መጠይቅ የሰጡንን መልስ ነው ከቤታቸው በሄድን በት ወቅት እንደአጋጣሚ ሆኖ ባለቤታቸው ስለሌሉ ለእርሳቸው ያቀረብንላቸው ጥያቄና መልስ ባይኖርም አብረው በኖሩበት ወቅት የተለየ ታሪክ እንደሌላቸው አባ ጐሹ ገልጸውልናል ።

አባ ጐሹ ዕድሜዎ ስንት ነው ? ሰማንያ ስምንት አመቴ ነው የባለቤትዎንም ዕድሜ መግለጽ ይችላሉ በሚገባ እኔ የምበልጣት በአራት ዓመት ነው እሉ ሰማንያ አራት ዓመት ማለታቸው ነው ። እኒሁ ሰማንያ ስምንትና ሰማንያ አራት ዓመት አለን የሚሉት አዛውንቶች ስልሣ ስድስት ዓመት የጋብቻ ዕድሜ አብረን ኖረናል ይላሉ ይህንንም የተነገረንን ዓመተ ምህረት ካለንበት ዘመን ጋር ስናስተያየው ልክ ሆኖ አግኝተነዋል አባ ጐሹን እንደገና ቀደም ካለው ታሪካቸው እንዲጀምሩ ለጠየቅናቸውም እንዲህ ብለዋል ።

ቀደም ሲል በነበረው የሀገራችን ወግ መሠረት በሐረርጌ በተወለድኩበት ማለት ነው መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የአማርኛ ትምህርቴን በመጀመር እዚያው ፈጽሜ ዳዊት ደገምኩ ከዚያም ዲቁና በመቀበል ሳገለግል ቆየሁ ይህ በእንዲህ እያለ ዕድሜዩ ለአቅመ አዳም ሲደርስ በአሥራ ዘጠኝ ዓመቴ መሆኑ ነው በሥጋወ ደሙ ና በተክሊል የአሥራ አምስት አመት እድሜ ከነበራት የዛሬዋ እማሆይ ፀዳል ጋር ጋብቻዩን ፈፀምኩ ከተጋባን ሦስት አመት በኋላም ቀሰስኩ የኑሮን ቀንበር እንዲህ እየተጓዝንበት አሥራ ሁለት ልጆች ወለድን ከእነሱም ለእኛ እንዲሆኑና በሕይወት እንዲቆዩ ባርኮ የሰጠን እኩሌቶቹን ብቻ ነው ከተረፉት ልጆች ጋር ግን ብዙ ሆነናል ብለውናል ልጆቻቸውን በማሳደግ እቁም ነገር እስቲያደርሱ ደርሶባቸው የነበረ ችግርም እንዳለ ለጠየቅናቸው እንዴ?ችግርማ ለምን ይጠፋል አሀያ እየጫንኩ ነዋ ያሳደኳቸው ብለዋል ።



66 ዓመት የጋብቻ ዕድሜ ያላቸው
እማሆይ ፀዳለ ዘወልዱና አባ ጐሹ ዋሴ

በዚህ የቤተሰብ ኑሮአቸው ያደርጉአቸው የነበሩ ሥራዎችንና ሁኔታዎችን በሚመለከት ለጠየቅናቸውም

ቤተሰብን ለማስተዳደር የሚያስችሉኝን ሥራዎችን መሥራት ልጆቻችንን ለማሳደግና ራስ ለማስቻል እኔም ሆንኩ ባለቤቴ የምናደርገው ጥረት እጅግ ነበር በተሰጠኝ የአገልግሎት ጸጋና በተቀበልኩት ሥልጣነ ክህነት በፍጹም ፍቅርና ስሜት ነበር እግዚአብሔርን ሳገለግል የቆየሁት ጥቂት ያህል የሆኑ መንፈሳውያን ቦታዎችንም አውቃለሁ ከእነርሱም መካከል ደብረ ሊባኖስ ብዙ ጊዜ እየሄድኩ ተሳልሜአለሁ ግሸን ማርያምንም እጅ ነስቻለሁ ኢየሩሳሌምንም አይቻለሁ ብለዋል ።

አሁን እንዴት እንደሚኖሩና ስለ ጠቅላላ ቤተ ሰቦቻቸው ቀጠል በማድረግ እኔ አሁን ቅድመ አያት ሆኛለሁም ከንያቱም ካሉኝ ስድስት ልጆች ስልሣ ሁለት የልጅ ልጆች አይቻለሁ የልጆቼም ልጆች አያት ለመሆን እየበቁ ነው ማለት ነው እነርሱም በተለያዩ ክፍላተ ሀገር ኑሮአቸውን መሥርተው ይኖራሉ፣

አባ ጐሹ ይላሉ ከባለቤቴ ጋር ለስልሳ ስድስት ዓመት ስኖር ያገኘናቸውን ልጆቻችንን በመመልከት ፈጣሪያችንን እያመሰገን አሁንም በአንድነት እንኖራለን ።

በቤተሰቦቻቸው መካከል ስለአሳለፉአቸው አንዳንድ ሁኔታዎች እንዳለ ለጠየቅናቸውም ይህን ያህል ዓመት ለኔም ሆንኩ ባለቤቴ ስንኖር የጠብም ሆነ የመለያየት ነገር አናውቅም እርስ በእርስ ተለያይተን ያደረግነው እኔም ሆንሁ ባለቤቴ የለብንም ተለይቼ አደርኩ የምለው ቢኖር ከማገለግልበት ቤተ ክርስቲያን መክፈልት መቅመሴን ነው ሌላ ሌላው ግን ጠላት በገባ ጊዜ ለጥቂት ጊዜ ዘምቻለሁ ይኸንን በሚገባኝ ቦታ ስለሆነ ተለየሁ አልለውም በኋላም በአንድ ነት የመኖራችንን ተስፋአድሶልን እነሆ አሁንም በሕይወት እንኖራለን የሚጠሩንም ልጆቻችን ናቸው ኑሮአችንም ፍጹም በሆነ ሰላምና ፍቅር የተሞላነው አሁንም እነሆ ከባለቤቴ ጋር መንኩሰን የልጆቻችንን ልጆችና የልጅ ልጆች በማየት እግዚአብሔር ለእኛ ያደረገልንን ሁሉ በጥሞና ለማሰብ እንድንችል ይህቺን ጊዜ ስለሰጠን ለእርሱ ክብርና ምስጋና አይለየው እያልን እንኖራለን ለልጆቻችን የምናስተላልፈው ቢኖር እግዚአብሔር ተርፎ ከሚፈሰው ዕድሜ እንዳይነፍጋቸውና የእኛን ዕድሜእንዲለግሳቸው ለንስሀ እንዲያበቃቸው ፀሎታችንነው ብለዋል ።



# ይህን ያውቁ ኖርዋል ?

እጅጉ ረታ

በጥንቱ ዓለም ታላቅነታቸው በታሪክና በመጽሐፍ ቅዱስ ገኖ ከተነገረላቸው ሀገሮች አንዱ የአሦር መንግሥት ነው ። የአሦር መንግሥት መዲና ነነዌ ከክርስቶስ ልደት በፊት በ2000-3000 ዓመት መካከል ባለው ጊዜ ውስጥ ተቆርቁራለች ። ይችን ከተማ የቆረቆራት የኩሽ ልጅ ናምሩድ መሆኑ በመጽሐፍ ቅዱስ ተጠቅሷል ። (ዘፍ.ም.10 ቁ.11-12) በባቢሎን ከተማና በነነዌ መካከል ያለው ርቀት 480 ኪሎ ሜትር ሲሆን ሁለቱ ከተሞች በየዘመናቱ ሁሉ ተፎካካሪዎች ነበሩ ። የአሦር መንግሥት እንደ ኤውሮፓ አቆጣጠር በ782 ዓመት ከልደተ ክርስቶስ በፊት ገኖ ባካባቢው ያሉትን ሀገሮች በሥልጣኑ ጫማ ሥር አውሏቸዋል ። በግዛቱ ላይ ከደረባቸው ሀገሮች አንዱ ከሁለቱ ነገድ ተለይተው አስሩ ነገድ ለብቻ ያቆሙት የሰሜኑ የእሥራኤል መንግሥትና የባቢሎን መንግሥት ይገኙበታል ። 630 ዓመት ከልደት በፊት ላይ የነበሩ ታላላቅ የዓለም ከተሞች በነነዌ ዐይን ሲታዩ እንደአንዳንድ ትንንሽ መንደሮች የሚቆጠሩ ነበሩ ። ከዚያም የተነሳ ነነዌ የዓለም መዲናዎች ቁንጮ "ንግሥት" ተብላ በታሪክ ተጠርታበታለች ። የነነዌ ከተማ በወርድ 16 ፣ በቁመት 48 ኪሎ ሜትር ያህል ሲሆን ይህም ርዝመቱ ከአዲስ አበባ ደብረ ዘይት ይደርስ ነበር ማለት ነው ። የነዋሪዎቿም ቁጥር አንድ ሚሊዮን ያህል እንደነበር ተገምቷል ። ከውጭ ወራሪ ስጋት ለመዳን ሲባል ነነዌ በአምስት ዙርያ ድርብ የግንብ አጥሮች ታጥራለች ። በተለይም 15 ኪሎ ሜትር ካሬ የሆነው የነነዌ መሐል ከተማ (እምብርት) ቤተ መንግሥቱ ያለበትና የጦር ኃያላኑ ሹማምንት የሚኖሩበት ክፍል በመሆኑ ቁመቱ 33 ሜትር በሆነ ግምብ ተከቧል ። ከግንቡ ውፍረት ወይም ስፋት የተነሳ ፣ በላዩ (ጫፉ) ላይ 4 የፈረስ ሠረገላዎች ጎን ለጎን ሆነው በአንድነት ይሄዱበት ነበር ይባላል ።

ነነዌ በታላላቅ የግንብ አጥሮች ሕንፃዎች በሀብት ጥሪትና በመሳሰሉት ሁሉ ከሌሎቹ ልቃ ልትገኝ የበቃችው በወራሪነት ከውጭ አፍልሳ ባመጣቻቸው የምርኮ ሀብትና በምርኮኞቹ ድካምና ላብ መሆኑ እዚህ ላይ ሳይጠቀስ ሊታለፍ አይገባውም ። የነነዌ ዘመናዮች ተድላ ደስታቸው እንዳይጓደል ፣ምርኮኞቹን ያለ ዕረፍት ሌት ተቀን እንዲሠሩ በማድረግ ያስገድዳአቸው ያስጨንቁአቸው ነበር ። ከድካማቸው ጽናት የተነሳ ፣ እጅ እግራቸው ዝሎ መሥራት የተሳናቸውንም ለሌሎቹ ማስፈራርያና መቀጣጫ ለማድረግ እጅና እግራቸውን ያለ ርኅራኄ በመቁረጥ ዐይናቸውን በማፍሰስ ገላቸውንም በቁመናቸው ገፎ ቆዳውን በማውጣት ለሕሊና የሚሰቀጥጥ ለጆሮ የሚቀፍ የጭካኔ ተግባር ይፈጽሙባቸው ስለነበር ልዑል እግዚአብሔር ሊያጠፋቸው ካሰበ በኋላ ለሕፃናቱና ለእንስሳቱ(ምንም ለማያውቁት) ስላዘነላቸው ዮናስን በ785 ዓመት ከክርስቶስ በፊት ልኮላቸው ለጊዜው ደንግጠው በንስሐ ተመልሰዋል ። በኋላ ግን የፈጣሪን ይቅርታና ምሕረት ዘንግተው ከፋታቸው እየፀና እየበረታ በመሄዱ ከደቂቀ ነቢያት አንዱን ናሆምን በ630 ከልደት በፊት አስነስቶ ነነዌ እንደምትጠፋ ትንቢት ተናግሮበታል ።ትንቢቱ በተነገረ በ20 ዓመቱ የፋርስና የሜዶን ሠራዊት ዘምቶባታል ። ቅጥሮቿን ጥሶ ለመግባት አልሆንለት ስላለውም ለሁለት ዓመት ከቦ መውጫ መግቢያ አሳጥቶ ካስጨነቃት በኋላ በድንገት የጤግሮስ ወንዝ ስለሞላ ፣ ከአንድ በኩል ያለውን የግንብ አጥር ሲንድለው በመቻሉ(ትን ናሆም 2፥6 ይመልከቱ) ይ ይህ ለወራሪው ሠራዊት መግቢያ ሆኖት ተመልሳ እንዳታንሠራራ አድርጐ ልክ በተነገረው ትንቢት መሠረት (ምዕ. 3፥1-7) አጥፍቷታል ።

በነቢዩ ፣ "...................... ባድማና ምድረ በዳ ትሆናለች ............

በተባለውም መሠረት ጨርሳ ጠፍታ ስለነበር በተከታዮቹ ቅርብ ዘመናት እንኳ ፣ የነበረችበትን ቦታ ለይቶ ለማወቅ እንዳልተቻለ በታሪክ ተመዝግቧል ።ለምሳሌ ታላቁ እስክንድር በ331 ዓመት ከክርስቶስ በፊት ዳርዮስን ገጥሞ ድል ወዳደረገበት "አርቤላ" ወደ ተባለው ስመ ጥፎ የጦርነት ሜዳ ሲገሠግሥ ፣በዚች ባድማ ቦታ አልፎ ነበር ። ከጠፋች ገና ሦስት መቶ ዓመት ብቻ የሆናት ታላቋ የነነዌ ከተማ ፣ የነበረችበት ቦታም ንም ዓይነት የከተማ ፍራሽ ምልክት ስላልነበረበት ቀድሞ በዚያ ቦታ ከተማ መኖር አለመኖሩን ለማወቅ አልቻለም ነበር ። ይህ በእንዲህ እያለ እያሌ ምዕት ዓመታት ካለፉ በኋላ ስለ ገናናው የአሦር መንግሥትና ስለ መዲናይቱ ስለ ነነዌ ከተማ ታላቅነት ብቻ ሳይሆን ፣ እንዲያውም ከናካቴው እንዲህ ያለ ገናና መንግሥትና ከተማ በዚች ምድር ላይ እንደነበረ የሚያረጋግጥ ወይም ፍንጭ ሊሰጥ የሚችል አንዳችም ዓይነት ተጨባጭ ምልክት (የታሪክ ቅሬታ) በምድሩ ላይ ሊገኝ ስለማይችል ስለ ነነዌ ከተማ በመጽሐፍ ቅዱስ የሚገኘው ታሪክ ከተረትና ከጥሩ የልብ ወለድ ፈጠራ ድርሰት የላቀ ግምት ሊሰጠው አይገባም ብለው በድፍረት የጻፉም የተናገሩም እንደነበሩ የታወቀ ነው ። ይሁን እንጂ እንደ ኤውሮፓ አቆ. በ1820 ዓ.ም ክለውድጀምስ እንዲሁም በ1845 ዓ.ም. ላያርድ ባደረጉት ጥረት የነነዌ ከተማ የነበረችበት ቦታ ሊገኝ ተችሏል ። በተከታታዮቹ ዓመታት በተደረጉትም የአርኪዎሎጂ ጥናትና ምርምር የነገሥታቱ የነሰናክሬም የነአሱርባኒፖል ቤተ መንግሥት ፍርስራሾች ተገኝተው ወጥተዋል ። ይልቁንም ከአንድ የቤተ መጻሕፍት ፍራሽ ውስጥ ከተገኙት 100000 የሸክላ ሰሌዳ መጻሕፍት ውስጥ ጥቂቶቹ የስነፍጥረትን አመጣጥ ልክ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አተራረክ የሚያቀርቡ ሆነው በመገኘታቸው ዛሬ በብሪትሽ



www.ethiopianorthodox.org


ሙዝየም የክብር ሥፍራ ተሰጥቷቸዋል እነሆ ዛሬ የነነዌ ከተማ ባዶ ምድረ በዳ ስለሆነች ዘወር ብሎ ማንም የሚያይት የለም ። ይህም በነቢዩ በናሆም የተነገረ ው ትንቢት በትክክል በመፈጸሙ ለመ ጽሐፍ ቅዱስ ታላቅነትና ለቃሉ ትክክ ለኛነት ማስረጃ ሆነው ከሚቀርቡት ነ ገሮች አንዱ በነነዌ ከተማ ላይ የተነገረ ው ትንቢት ሆኖ እናገኘዋለን ።

## የኤርምያስ ጉድጓድ.....

ከገጽ ፲፱ የዞረ

ርምያስን ጉድጓድ እንዲጐበኙ በአንድ መነኩሴ ተወስደው ነበር ከዚያን ጊዜ ወዲህ ግን የቆሻሻ መከማቻ ቦታ ሆኖ አል ። ከመስቀል አርበኞችና ከእነርሱ ም በኋላ የአዮባን ሐረገ ትውልድ የእስ ላም ሱልጣኖች ወደ ሰሜን በኩል እራ ቅ ብሎ የሚገኘው የከተማውን ግድግዳ እንደገና ገነቡት ፣ የኤርምያስም ጉድጓ ድ በእሥራኤላውያን አርኪዮሎጅ ስቶ ች አካፋ እስከተገለጠበት ቅርብ ጊዜ ድረስ በተነባበሩ ቆሻሻዎች ተሸፍኖ ይኖር ነበር ።

ለረዥም ጊዜ ጠፍቶ ወይም ተሠወ ሮ የኖረው የኤርምያስ ጉድጓድም በመ ጨረሻ ሊታይ ችሏል ። ይህም ከባዛንታ ይን መታሰቢያ ጋር በማመሳከር ነው ። በግምት ለጲላጦስ ፕሪቶሪየም ቀረብ ብ ሎ የሚገኘውን የኤርምያስን ጉድጓድ ለ አምልኮት የመረጡት ይመስላል ፣ ምክ ንያቱም የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያ ናት የኤርምያስን ስቃይ ከክርስቶስ መ ከራ ጋር አዛምደው ይጠቅሱታል (ያዩ ታል) በትክክል ኤርምያስ የተጣለበት የውኃ መያዣያ ጉድጓድ የት እንደነበር እግዚአብሔር ብቻ ነው የሚያውቀው ከኢየሩሳሌም ስደት አስቀድሞ ስለነበ ረው እንኳን የባዛንታይን አቀማመጥ የ ሚመስል ሀሳብ አለው ። ሊሆን ይችላ ል ። ከሆነስ ባዛንታውያን እውነተኛ ውን ጥንታዊ የአይሁድን ባሕል ተከት ለዋልን?


ኢየሩሳሌም ከ6-10ኛው፡ ክፍለ ዘመን፡

አንዳንድ አሮጌ ግድግዳዎች ከጉድጓ ዱ መግቢያ አጠገብና በባዛንታይን ሥ ር የቫሌ ካርድ መንገድ አልተቆፈሩም። የማልኪው የዘበኛ ቤት ነበር ኤርምያስ 38፡6

በጥንቱ የባዛንታይን ዘመን የይሁዲ መመሪያዎች የክርስቲያን ተሳላሚዎች የሥራ መመሪያ ሆኖ ተገኝቷል ። የአም ልኮትን ሥነ ስርዓት ለክርስቲያን አድ ማጮቻቸው ያስተላልፉ ነበርን? የቦታ ው ጥልቅ ምርምር ለዚህ መልሶችን ሊ ሰጥ ይችላል ፣ የጥንታዊት ኢየሩሳሌም ን ጠቅላላ ሁኔታ በሚመለከት ሌሎች ጥያቄዎችን ጭምር ሊመልስ ይችል ይ ሆናል ።

ክርስቲያን ንውስ ከተሰኘው በእሥ ራኤል አገር ከሚታተመው እንግሊዝኛ መጽሔት ቅጽ 26 ቁ.3 1980 (እ.ኤ.አ) ተተረጐመ

ተርጓሚ ከፍያለው መራሂ



# ልማት በቤተ ክርስቲያን

በቤተ ክርስቲያን ቅጥር ግቢ ትም ህርት ቤቶችን በመሥራት ሕፃናትን ሰብስቦ በማስተማር የመጠለያ ቤቶችን ም በመሥራት አካለ ስንኩሎችንና ዓይነ ሥውሮችን መርዳት ሀገርንና ወገንን መርዳት ነው በዚህም አጥጋቢ ፍሬ ከመገኘቱም በላይ በእግዚአብ ሔርም ዘንድ ዘለዓለማዊ ሕይወት የሚ ያድል ነው ይህንንም መሠረት በማድ ረግ በወለጋ ክፍለ ሀገር በግምቢ አው ራጃ ርእሰ ከተማ በመድኃኔ ዓለም የሰ በካ ጉባዔ ሊቀ መንበር አቶ ንጉሣ ፈይሳን በቤተ ክርስቲያኑ ቅጥር ግቢ ምን ዓይነት ልማት እንደተቋቋመበት አነጋግረናቸው ነበር ።

ትንሣኤ ፣ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን በቅድሚያ ያስፈልጉ አታል ከሚባሉት ነገሮች አንዱ ልማት መሆኑ በሁሉም ዘንድ የታወቀ ነው ።

በዚሁ መሠረት በግምቢ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን አካባቢ የተቋቋ መ ልማት አለ?

አቶ ነጋሣ ፈይሳ አዎ በዚህ በግምቢ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን አካባቢ በመጠኑ የጀመርነው ልማት አለ ይኸ ውም 1ኛ 4 ክፍል ያለው ት ቤት አሠር ተን በእነዚህ ክፍሎች ውስጥ ከ 200-250 ድረስ ብዛት ያላቸው ሕፃናት ዕው ቀት ሲገበዩበት መንፈሳዊ ጥበብንም ሲሸምቱበት ይታያል ።

2ኛ በዚህ በግምቢ አውራጃ ዋና ከተማ አካለ ስንኩ ሎች ስለሚገኙና እነሱም መጠለያ አጥተው በቀን ሐሩር በሌሊት ቁር ከመሰቃየታቸውም በላይ በክረምትም ቢሆን የሚወርደው ዝናብ በላያቸው ላይ ያርፍ ስለነበር ለእነሱ መጠለያና ለብርድ መከላከያ የሚሆና ቸው 30 የሚሆኑ መጠነኛ ቤቶች ከጀ ርመን ተራድኦ ጋር በመተባበር ሠር ተን እነሆ ከአንድ መቶ በላይ የሚሆኑ አካለ ስንኩሎች ከቤት እጦት ተላቅቀ ው ችግራቸውንም አስወግደው ይኖሩ በታል ።

ትንሣኤ ፣ 30 የሚሆኑ የመጠለያ ቤት ስትሠሩላቸው ምግባቸውንስ ማን ይመ ግባቸዋል ከዚህስ ሌላ እነሱ የሚሠሩት ሥራ አለ ወይ?

መልስ ፣ እነዚህ ሰዎች ዓይነ ስውሮችና አካለ ስንኩሎች እንደመሆናቸው መጠን ለቤተ ክርስቲያኑም ሆነ ለራሳቸው አን ድም ነገር የሚሠሩት ሥራ የላቸውም ስለ ምግባቸውም ቢሆን አንዳንድ ለነፍ ሳቸው ያደሩ ክርስቲያኖች ይመግቧቸ ዋል እንጂ ስለ ምግባቸው ሙሉ ድርጅት የተቋቋመ የለም ቢሆንም ለወደፊት አስፈላጊውን ነገር ሁሉ አሟልተን በሚ ገባ እንደ - ምንይዛቸው ተስፋ እናደርጋ ለን ።

ትንሣኤ ፣ አራት ክፍል ያለው ት ቤትና ከ250 በላይ የሚሆኑ ተማሮች መኖራ ቸውን ገልጸዋል እነዚህን ሕፃናት ለሚ ያስተምሩ መምህራን ደመወዝ የሚከ ፍላቸው ማን ነው?

መልስ ፣ ለመምህራኑ ደመወዝ የሚከ ፍላቸው ቤተ ክህነት ነው?

ትንሣኤ ፣ ለመሆኑ ይህንን ት ቤት ስትሠሩ ለት ቤቱ ማሠሪያ የሚሆን ከቤተ ክህነት ያገኛችሁት ገንዘብ አለ?

መልስ ፣ ይህንን ት ቤት ስንሠራ ከቤተ ክህነት ያገኘነው የገንዘብ እርዳታ የለ ም እኛም ት ቤት እን ሠራለንና በገን ዘብ እንድታግዙን ብለን አልተናገርንም ቢሆንም ምንም እንኳን ቤተ ክህነት ገንዘብ ባይሰጠንም በጸሎት ከእኛ ሳይ ለይ እንደሚያስበንና በጸሎት እንደሚ ረዳን ተስፋችንና እምነታችን ጽኑ ነው።

ትንሣኤ ፣ በዚህ በግምቢ መድኃኒ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስንት አገልጋ ዮች ይገኛሉ?

መልስ ፣ በግምቢ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ካህናት ዲያቆናትና መዘምራን በጠቅላላ 25 ይሆናሉ እነዚ ህም በቅዳሴም ሆነ በማህሌት ቤተ ክር ስቲያ ኑን ሲያገለግሉ ምእመናንንም ሲያስተምሩ ይገኛሉ ።

ትንሣኤ ፣ እነዚህ 25 የሚሆኑ የቤተ ክር ስቲያንስ አገልጋዮች በደመወዝ ነው ወይስ በነጻ ነው የሚያገለግሉ ።

መልስ ፣ በቂ ደመወዝ ነው ተብሎ ባይ ታመንም ቤተ ክርስቲያኑ ባለው ዓቅም መጠነኛ ደመወዝ አላቸው ይኸውም በግምቢ መድኃኔዓለም የተቋቋመ የሰ በካ ጉባዔ ስ ላለ የሰበካ ጉባዔ ነው ደመወዛቸውን የሚከፍላቸው ።

ትንሣኤ ፣ በቤተ ክርስቲያን በኩል ያጋ ጠማችሁ ችግር ይኖራልን?

መልስ ፣ የግምቢ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን በሚገባ በሰበካ ጉባዔ የተደ ራጀ ቢሆንም እንኳ አንዳንድ ችግር ሳያጋጥመን አልቀረም ይኸውም በሌላ በኩል የጐደለን ሳይኖር ሀገሩ በረሐ በመሆኑ በየደብሩ እየተዘዋወሩ የሚያስ ተምሩ መምህራን ያስፈልግ ነበር እኛ እንዳንቀጥር ዓቅማችን የማይፈቅድ ልን ሆነ ስለዚህ የመምህራን እጦት ካልሆነ በስተቀር በሌላ መንገድ በቤተ ክርስቲያን ያጋጠመን ችግር የለንም ።

ትንሣኤ ፣ በግምቢ አውራጃ ስንት አብ ያተ ክርስቲያናት ይገኛሉ?

መልስ በግምቢ አውራጃ ውስጥ 240 የሚሆኑ አብያተ ክርስቲያናት ይገኛሉ እነዚህም በከተማው ውስጥ ሦስት አብያተ ክርስቲያናት በሰበካ ጉባዔ የተደራጁ ሲሆኑ ከከተማ ውጭ ደግሞ በሰበካ ጉባዔ የተደራጁና በሰበካ ጉባዔ ያልተደራጀ 237 ይገኛሉ ።

ትንሣኤ ፣ ስለ ቤተ ክርስቲያን አስተ ዳደር ማሻሻል ለወደፊት ያላችሁ ዕቅድ ምንድን ነው ።

መልስ ፣ የወደፊት ዕቅዳችን አንደኛ ከዚህ በፊት የሠራነውን ትምህርት ቤት ለማስፋፋትና በሚገባ ለማደራጀት ሰፊ ዕቅድ አለን ይሁን እንጂ የሚሠራው ሥራ ሁሉ ያለ ክርስቶስ ፈቃድ ስለማይ ፈጸም የክርስቶስን ረድኤት ተስፋ እያደ ረግን ብዙ ያቀድነው ዕቅድ አለን



www.ethiopianorthodox.org

ትንሣኤ ፣ ቤተ ክርስቲያኑ ከውስጥም ሆነ ከውጭ የሚያገኘው ገቢ አለው ? መልስ ፣ ቤተ ክርስቲያኑ በሙዳየ ምጽዋት ከምእመናን ከሚገባው መባ በስተቀር ከውስጥም ሆነ ከውጭ የሚያገኘው ገቢ የለውም ።

በእውነቱ ስንመለከተው መሣሪያ ሳይዝ ወደ ዘመቻ የሚሄድ ሰውና በእካባቢዋ ት ቤት የሌላት ቤተ ክርስቲያን ልዩነት የላቸውም አንድ ናቸው ለማለት እንደፍራለን ምክንያቱም የቤተ ክርስቲያን አለኝታ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ነውና በተለይ በወሊጋ ክፍለ ሀገር በነቀምቴና በአሱሳ አውራጃዎች አስተዳደር ውስጥ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ በድርቅና በልዩ ልዩ የተፈጥሮ ነገሮችምክንያት መንግሥት ያሰፈራቸው ሰዎች አሉ እነዚህም ሰዎች በሰፈሩበት ሁሉ በተለያዩ ቦታዎች 17 አብያተ ክርስቲያናት ተሠርተዋል ታድያ እነዚህን ሰዎች የሚያስተምሩ መምህራን ካልተመደቡላቸውና በሃይማኖት ጸንተው እንዲኖሩ ጥረት ካልተደረገላቸው የተሠሩት አብያተ ክርስቲያናት ዋጋ እንደማይኖራቸው ከዛሬ ጀምሮ ቢታሰብበት መልካም ነው እንጋለን ።

ክንፈ ርግብ ማርቆስ

## ደብዳቤዎች

ከገጽ ፲፯ የዞረ

በፖስታ ሐዋላ 3137 ወይም ከቢሮአችን ድረስ መጥተው ቢከፍሉ ሊደርስዎ ይችላል ። ካልቻሉ ያንዱ ማኅበርተኛ መሆንም ይቻላል ።

7ኛ የወጣቶች ጉዳይ መምሪያ ኃላፊ ችግር ያለባቸውን ቦታዎች ከተረዱ እየተዘዋወሩ ችግሮችን የመፍታት ኃላፊነት አለባቸው ስለሆነም እርሳቸው ጥያቄውን ተመልክተው መፍትሔ እንዲሰጡት ጥያቄዎን አውጥተነዋል ።

8ኛ የቅዳሴ ዓይነቱ ሲሉ ግልጽ አልሆነልንም ምንአልባት ብዛቱን ከሆነ የጠየቁት በቤተ ክርስቲያናችን 14 ቅዳሴያት አሉ የዜማውን ዓይነት ከሆነ ያሉት ሁለት ናቸው እነርሱም እዝልና ግዕዝ ።

9ኛ በጾም ወቅት ዓሣ መብላት ተፈቅዶአልን?ለሚሉት ፍትሐ ነገሥት ነጠላ ትርጉም ይበላል ሲል አንድምታው ግን አይበላም ይላል ለዚሁም ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 15 ቁጥር 572 ይመልከቱ ።

10ኛ ሰው ከመነኮሰ በኋላ ምን ማድረግ አለበት ለሚለው የመነኮሰበትን ዓላማ መፈጸም ነው

## ቅዱስ ሲኖዶስና .....

ከገጽ ፰ የዞረ

የተጠኑ የማያዳግሙ ለካህናትና ለምዕመናን የሚስማሙ እንዲሆኑ ያስፈልጋል ።

ርክበ ካህናትም ቢሆን የቤተ ክርስቲያንን ህልውና ለማስጠበቅ ታላቅ አገልግሎትን ስለሚያበረክት ምንም እንኳን በአሁኑ ጊዜ ስሙ እንጂ ሥራው አለመኖሩ ቢታወቅም ካህናት እየተሰበሰቡ ስለቤተ ክርስቲያን የሚወያዩበት የተወሰነ ቦታ ቢኖር ለቤተ ክርስቲያናችን ከፍ ያለ መንፈሳዊ አገልግሎት የሚያበረክት መሆኑ አያጠራጥርም እላለሁ ።

ቄስ ልሳነ ወርቅ በዛብህ



# ኢ.ኦ.ተ.ሐ.ድ

ማሳሰቢያ ለምእመናን በሙሉ

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፣ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፡ መንፈሳዊ ዘመናዊ መዝሙሮችን ፣ ትምህርቶችንና የልማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየተከታተለ በቴፕ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅርስ ያስቀምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴት ክር ላቀረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ በማስከፈል ይሰጣል ።

ለዚሁ ጥያቄ ቢኖርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመረዳት ይቻላል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሐዋርያዊ ድርጅት
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት

ስልክ ቊ. 116616
የመል. ሣ. ቊ. 3137
አዲስ አበባ

www.ethiopianorthodox.org